ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “በኋላ ዘመን የሐሰት ነቢያት ይነሳሉ ፡ ብዙዎችን ያስታሉ” ሲል በሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ሸህ አህመድ ዲዳት የጻፋቸው መጣጥፎች ሁሉ የክርስትናውን ዓለም የሚፈታተኑ ናቸው ፤ የመልስ መጻሕፍ ቱም በሥነ መለኮት ትምህርታዊ ብቃታቸው በመልስ ሰጭነታቸው አጥጋቢና አስተማማኝ በመሆናቸው በኢትዮጵያዊኛ ቋንቋ ብቻ ሳይወሰኑ ዓለማቀፋዊ እውቅና እንዲኖራቸው

ሀ/በእንግሊዝኛ ቋንቋ

ለ/ በዓረብኛ ቋንቋ ይታተሙ የሚል አስተያየት ከያቅጣጫው እየቀረበ ነው ፡ በዚህ መሠረት በተለይ “መጽሐፍ ቅዱስና መሐመድ አይተዋወቁም” የተሰኘው የመልስ መጽሐፍ በቅርብ ጊዜ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ታትሞ እንደሚወጣ ላረጋግጥ እወዳለሁ ።

# አዎ፣ ኢየሱስ ፈጣሪ ነው!

ከመምህር ኪዳነ ማርያም ጌታሁን

ለአህመድ ዲዳት የተሰጠ መልስ

አዲስ አበባ፣ 1990 ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

«በሰው ፊት ያመነብኝን ሁሉ እኔም በሰማያት ባለው አባቴ ፊት አምንበታለሁ፤ በሰው ፊትም የካደኝን እኔም በሰማያት ባለው አባቴ ፊት እክደዋለሁ» (ማቴ.10፥32)።

✣ ✣ ✣

«እኔ መንገድ ነኝ፥ እውነትም ሕይወትም፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» (ዮሐ.14፥6)።

✣ ✣ ✣

«እኔ ነኝ፥ አልፋ ያሜጋ መጀመሪያ መጨረሻም፤ የፊተኛውም የኋለኛውም» (ራእይ 22፥13)።

✣ ✣ ✣

## ምስጋናዬ ይድረሳቸው

1ኛ. መጀመሪያውን ማለት «መጽሐፍ ቅዱስና ሙሐመድ» የተሰኘውን፤

2ኛ. ይህን «ክርስቶስን ከቁርአን ጋር ምን አገናኘው» የተሰኘውን፤

እነዚህን ሁለት የመልስ መጻሕፍት ከመታተማቸው በፊት በግል አንብበውና በተለይ የመጀመሪያውን ጽሑፍ በሌሎች ሰዎች እንዲገመገም ካደረጉ በኋላ በመልስ አሰጣጡም ሆነ በትምህርት ሰጭነቱ አጥጋቢ ሆኖ ስላገኙት የማሳተሚያውን ገንዘብ ኀመለገስ ሁለቱም ድርሰቶች በተከታታይ ታትመው ለምንባብ እንዲበቁ ያደረጓቸው በጎ አድራጊ ምዕመን ኰሎኔል እምላዕሉ ወረደ ናቸው። እኚህ ውድ የቤተ ክርስቲያን ልጅ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመኑ የነበሩትን ፈታኞች ፈሪሳውያን «ለቄሣር ግብር መስጠት ይገባልን?» በማለት ላቀረቡለት ጥያቄ ገንዘቡን አይቶ «የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ» ሲል የሰጣቸው መልስ አስተኔ መመሪያ የተከተሉ፤ ገንዘባቸውን ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን ግንባታ ያዋሉ (ገብር ኄር ወምዕመን) ታማኝ አገልጋይ ናቸው፤ ለእነዚህ ሕይወት አልባ ሆነው ለተወለዱ ድርሰቶቼ በቀዶ ጥገና የሕይወት እስትንፋስ ሰጥተው ባፋቸው እንዲናገሩ፤ የክርስቶስን አምላክነትና አዳኝነት ባደባባይ እንዲመሰክሩ ያደረጓቸው ሐኪም እምላዕሉ ወረደ ናቸው፤ ለኚህ የክርስትናው ኅብረተሰብ ታላቅ ባለውለታ ምዕመን የማቀርብላቸው ምስጋና ወደር የለውም።

እንደዚሁም አንድ በጎ አድራጊ በለገሱኝ ገንዘብ የኮምፒዩተር ሙያ ያላቸው ሌላው በጎ አድራጊ ድርሰቱን በኮምፒዩተር ቀርፀው ፊደሉን በጥንቃቄ አርመውና መጽሐፉ በሥነ ጽሑፍ ይዘቱ የተዋጣለት እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስላደረጉልኝ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው።

እንዲሁም ወይዘሮት አስጉ መንግሥቱና ወይዘሪት ፀዳለ ተክሌ የእጅ ጽሑፉን ታይፕ በማድረግ ስለ ረዱኝ ባለውለታዎቼ ናቸው፤ አመሰግናለሁ።

ያለ ደራሲው ፈቃድ መልሶ ማሳተም (መተርጐም) ክልክል ነው።

# ማውጫ


- መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
- መቅድም . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6

ክፍል አንድ

- ኢየሱስ እውን ፈጣሪ ነውን? . . . . . . . . . . . . 9
- ሁለት መላምቶች . . . . . . . . . . . . . . 10
- ማጠቃለያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 38

ክፍል ሁለት

- ክርስቶስ ስም አይደለም . . . . . . . . . . . . 41
- የዮናስ ምልክት (ተአምር እንደማስረጃ) . . . . . . . 42
- ዓውደ ዓመት . . . . . . . . . . . . . . . . 44

ክፍል ሦስት

- ትንሣኤ ወይስ ማንሰራራት? . . . . . . . . . . . 47
- ልዩ ማስገንዘቢያ . . . . . . . . . . . . . . 49


www.ethiopianorthodox.org

# መግቢያ

መናፍቃን በየጊዜው እየተነሡ የእግዚአብሔርን አምልኮት ሲቃወሙና ሕልውናውን ሲፈታተኑ ኖረዋል፤ ፍጻሜያቸው ግን ውድቀት ነው። ለምሳሌ አርዮስንና ንስጥሮስን መጥቀስ ይቻላል። አርዮስ ወልድ በመለኮቱ ፍጡር ነው፣ ፈጥሮ ፈጠረበት በማለት የተነሣ ከሐዲ ነው። ንስጥሮስም ድንግል ማሪያም የሰው እናት ናት እንጂ የአምላክ እናት አትባልም የሚል መናፍቅ ነበር፣ ሁለቱም አልቆዩም፣ ወዲያው ጠፍተዋል፣ የግብር ልጆቻቸው (መናፍቃን) ግን ከምድር ገጽ አልጠፉም።

ቀደም ሲል ኢየሱሳውያን ፤ጀስዊት የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት የሃይማኖት ጥገኛ ሊያደርጉት ብዙ ጊዜ ያልተሳኩ ሙከራዎችን አድርገዋል። ባንድ ወቅት ‹በጎንደር መንግሥት ጊዜ› አንድ የውጭ አገር መናፍቅ ከኢትዮጵያ ሊቃውንት ጋር የሃይማኖት ክርክር እንዲያደርግ ጠይቆ ሊቃውንቱና ሕዝቡ በተገኙበት ጉባኤ መጀመሪያ መናፍቁ እንዲጠይቅ ተፈቀደለት። ከተቀመጠበት ተነሣና «‹እግዚአብሔር በልጁ ሞት ታረቀን› የሚል ንባብ ከሐዲስ ኪዳን ውስጥ የት ይገኛል? አስረዱኝ» ሲል ጠየቀ። ከሊቃውንቱ አንዱ ተነሥቶ ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ምዕ. 6 ቁ.10 ላይ «እኛ የእግዚአብሔር ጠላቶቹ ስንሆን በልጁ ሞት ታረቀን» ይላል ሲል መለሰለት። መናፍቁ እንደገና ግራ «ለማጋባት የእግዚአብሔር ፊቱ ወዴት ነው?» ሲል ተራ ጥያቄ አቀረበ። ሊቁም ግራ ሳይጋባ ባደባባይ መብራት አብርቶ «የዚህ መብራት ፊቱ ወዴት ነው?» ሲል ጥያቄውን በጥያቄ መለሰለት። መናፍቁም ጥያቄው በጥያቄ ስለ ተመለሰለት ግራ



ተጋብቶ ዝም ብሎ ቆመ። በዚህ ጊዜ ሊቁ «የዚህ መብራት ፊቱ በዚህ በኩል ነው እንደማይባል የእግዚአብሔርም ፊቱ በዚህ በኩል ነው አይባልም፤ ምሉዕ በኩለሄ ነው» በማለት ካስረዳ በኋላ መናፍቃኑ በሰው አገር መጥተው በሚያስነሡት የሃይማኖት ብጥብጥ የተበሳጨው ምሑር ማስረጃው ይህ ብቻ አይደለም በማለት ከዳዊት መዝሙር «ገጹ ለእግዚአብሔር ኀበ እለ ይገብሩ እኩየ» ትርጕሙ፦ «የእግዚአብሔር ፊቱ ክፉ ወደሚሠሩ ሰዎች ነው» በማለት ፊቱን ወደ መናፍቁ መልሶ አንድ ጊዜ በጥፊ አጮለው ይባላል።

አሁንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደ አህመድ ዲዳት ያሉ ድንበር ዘለል መናፍቃን የአርዮስን ካባ ደርበው መጽሐፍ ቅዱስን አንግበው ክርስትናን ለመናድ ተከታዮቹን ለማወናበድ ዓለማቀፋዊ የክህደት ዘመቻ ከፍተዋል። የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ገጸ መዓቱን ከፉ ወደሚያደርጉ ይመልስባቸው ብለን አንጸልይባቸውም፤ መምህራችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመከራው ወቅት «የሚያደርጉትን አያውቁትምና ይቅር በላቸው» ሲል ለጠላቶቹ እንደ ጸለየላቸው እኛም ይህንኑ በመድገም መልካሙን እንመኝላቸዋለን።

www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም

እግዚአብሔር ለስሙ መጥሪያ ለአምልኮቱ መግለጫ እንዲሆኑ ከመረጣቸው አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ናት። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ቀደም ሲል እግዚአብሔር በነቢያት አድሮ ከክርስቶስ ልደት በፊት 2000 ዓመተ ዓለም ላይ «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» ሲል ኢትዮጵያን እግዚአብሔር የመረጣት ምን ጊዜም እግዚአብሔርን የምታመልክ እግዚአብሔርም የሚወዳት የአምልኮቱ መግለጫ ስለ መሆኗ አስቀድሞ ትንቢት አናግሮላታል። ከዚህ የተነሣ ከእስራኤል ቀጥላ የሙሴን ሕግ «ኦሪትን» የተቀበለች ባንድ አምላክ ያመነች በኦሪት ሕግና ሥርዓት 950 ዘመን ያህል እየተመራች የኖረች ሁለተኛ ሀገር ናት (መዝሙር 67(68)፥31)።

5500 ዓመተ ፍዳ፣ ዓመተ ኩነኔ ሲፈጸም ከሥላሴ አንዱ ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው ሆኖ ‹ሥጋ ለብሶ› ወንጌልን አስትምሮ ለሰው ልጆች ደኅንነት በመስቀል ላይ ሞቶ ከተነሣ በኋላ ኢትዮጵያ የተነገረው ትንቢት የተቈጠረው ሱባኤ እንደ ተፈጸመ አውቃ ሐዋርያ ሳይላክላት ኢየሩሳሌም ድረስ ሄዳ በክርስቶስ ስም ያመነች የተጠመቀች ቀዳሚት ሀገር ናት (የሐዋ.9፥26) ከዚህ የተነሣ በዓረቡ ዓለም የተከበበች ብቸኛ አፍሪቃዊት የክርስትና ደሴት እየተባለች ትጠራለች።

ከ600 ዓመተ ምሕረት በኋላ ሙስሊሞች ነቢያችን የሚሉት ሙሐመድ በዓረቡ ዓለም ውስጥ ተነሥቶ እስልምናን ሰበከ። ስብከቱም ለጊዜው ተቀባይ ባለማግኘቱ ከመካ ወደ መዲና ተሰድዶ ለአሥር ዓመታት ያህል ኃይሉን ካጠናከረ በኋላ ወደ መካ ተመልሶ ተቀዋሚዎቹን በማሸነፍ አዲሱን እምነት እንዲቀበሉ አድርጓል።



ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር አምልኮት መግለጫ ብቻ ሳትሆን በእንግዳ ተቀባይነቷም የተመሰከረላት ሀገር ናት። ሙሐመድ ይህን ሐቅ ተገንዝቦ ለተከታዮቹ መመሪያ ሰጥቷቸዋል። «እስላም በመሆናችሁና በሚደርስባችሁ ችግር ወደ ኢትዮጵያ ተሰደዱ፤ እዚያ የሚነግሠው ንጉሥ እርሱ ሰው የማይበድል በርሱ ዘንድ ሰው የማይበደልበት ደግ ነው» የሚል ነው። ከዚህ የተነሣ የሙሐመድ ቤተሰቦችና ጥቂት ተከታዮቹ ከተቃዋሚዎቻቸው በደረሰባቸው ተፅዕኖ ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው ጥገኞች ሆነዋል። ባላንጣዎቻቸው ተከታትለው እጃቸው እንዲሰጣቸው ቢጠይቁ፣ «ጥፋታቸው ምንድነው? ሰው ገድለዋልን? ወይስ ንብረት አጥፍተዋል?» ሲል ንጉሡ ጠየቃቸው። «ሰው አልገደሉም ንብረትም አላጠፉም፤ ሆኖም ስለምንፈልጋቸው እጃቸው ይሰጠን» አሉት። ንጉሡም፣ «ሰው ያልገደሉና ንብረት ያላጠፉ ከሆኑ ተላልፈው አይሰጡም» በማለት ተቃዋሚዎችን ወደ መጡበት መልሶቸዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ሙስሊሞች በባብዔል መንደብ በኩል ወደ ኢትዮጵያ መጉረፍ ጀመሩ ይባላል።

የሙስሊሙ ኅብረተሰብ አብሮ ከመኖር የተነሣ የክርስቲያኑን ኅብረተሰብ ባህልና አኗኗር፣ ሰላምና ትሕትና እየተላበሰ መጣ። በእስላሞችና በክርስቲያኖች መካከል አብሮ የመኖሩ ውሕደት እየጨመረ እንደ መሄዱ መጠን የመከራውንም ሆነ የደስታውን፣ የጦርነቱንም የነፃነቱንም ፅዋ አብሮው ሲቋደሱ ኖረዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ እስላሙና ክርስቲያኑ ኅብረተሰብ ከ1400 ዘመን በላይ አብረው ሲኖሩ በመካከላቸው ሃይማኖታዊ ግጭት ተነሥቶ አያውቅም፤ በቱርክ መንግሥት አነሳሽነትና ድጋፍ ሰጭነት በምሥራቅ ኢትዮጵያ በሐረርጌ ተነሥቶ የነበረው ግራኝ ሙሐመድ ሰሜን ሸዋን፣ ወሎን፣ ትግራይንና ጎንደርን ለጊዜው ተቆጣጥሮ እንደ ነበረ ታሪክ ያስታውሰናል። ይኸውም በውጭ መንግሥት ጣልቃ ገብነት እንጂ በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች መካከል እንደ ተደረገ ግጭት የሚቈጠር አይደለም፤ ምክንያቱም ግራኝ ሙሐመድ በፖርቱጊዞች ርዳታ ከሞተ በኋላ ወዲያው ጦርነቱ ቆሟል፤ የእርስ በርስ ግጭት ቢሆን ኖሮ ጦርነቱ ሊቀጥል በቻለ ነበር።

www.ethiopianorthodox.org

አንዳንድ የአፍሪቃ አምባባነን መሪዎች በሕዝባቸው መካከል በሚፈጥሩት አለ መግባባት የእርስ በርስ ግጭቶች እየተነሡ ወደ ከፋ ጦርነት ሲሸጋገሩ በኢትዮጵያ ግን ነባር መሪዎች ወድቀው አዲሶቹ ሥልጣን በያዙ ቁጥር እስላሙና ክርስቲያኑ ኅብረተሰብ ሰላሙን እና አንድነቱን ከመጠበቅ በስተቀር የጎሳም ሆነ የሃይማኖት ግጭት አድርጎ አያውቅም፤ የሱማሌን የላይቤርያንና የሱዳንን የእርስ በርስ ግጭት ያየና የሰማ ሁሉ በአንፃሩ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጨዋነትና አስተዋይነት እየተመለከተ ያደንቃል።

በዚህ ጭዋነታችንና ሰላማዊ ኑሯችን የቀኑብን ድንበር ዘለል አክራሪዎች የኢትዮጵያን ሕዝብ በሃይማኖት ለመከፋፈል ክርስትናን የሚነቅፍ እስልምናን የሚደግፍ መጣጥፍ እያሳተሙ በአዲስ አበባ ከተማ ማሰራጨት ከጀመሩ ውለው አድረዋል። ይህ የአክራሪዎች ሥውር ዓላማ ተቀባይ ይኖረዋል ብለን ባናምንም ለጽሑፋቸው ተገቢውን መልስ መስጠት አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። ቁርአንን የመተርጐምና የመተንተን መብት የሙስሊሙ ኅብረተሰብ ምሑራን የመሆኑን ያህል፣ መጽሐፍ ቅዱስንም መተርጐምና መተንተን የሚገባቸው እነዚያው የመጽሐፍ ሰዎች (የሥነ መለኮት ሊቃውንት) መሆን ሲገባቸው፣ እንደ አህመድ ዲዳት ያሉት መናፍቃን መጽሐፍ ቅዱስን በድፍረት እንደ ፈለጉ እያዛቡና እየጠመዘዙ በመተርጐም ሲያበላሹትና መቅኖ ሲያሳጡት ይታያሉ። ከባድ ስህተት ነው፣ ካሁን በፊት ቁርአንን ነቀፎ በድፍረት ከጻፈው ግለሰብ የማይተናነስ ብልግና ነው። በሃይማኖት መነቃቀፍ በሕዝብ መካከል አለመረጋጋትንና መከፋፈልን ‹መለያየትን› ያመጣል፤ መለያየት ደግሞ የመጨረሻ ውድቀትን ያስከትላል። «እርስ በርሷ የምትለያይ መንግሥት አትጸናም» (ማቴ.12፥25)።



ክፍል አንድ

«ኢየሱስ አውን ፈጣሪ ነው?»

# አዎ! ኢየሱስ ፈጣሪ ነው!

የጽሑፉ አቅራቢ «ኢየሱስ አውን ፈጣሪ ነው?» በሚል ርእስ ይጀምርና «በአላህ ስም እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው» ካለ በኋላ፣ «አንድ ፍጹም አምላክ ብቻ መኖሩን የሚያውጅ ሃይማኖት ቢኖር እስላም ብቻ ነው፣ አንድ ፍጹም አምላክ ሲባል ደግሞ በሁለንተናዊ ባሕርዩ ፍጹም አምሳያ ሸሪክ ‹ተጋሪ› የሌለው ብቸኛ አንድ አምላክ ማለት ነው፣ እርሱ አላህ አንድ ነው፣ አላህ የሁሉ መጠጊያ ነው፣ አልወለደም አልተወለደም፣ ለእርሱ አንድም ቢጤ የለውም» ይላል።

እኔም «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፣ ባንድነቱ ሁለትነት፣ በሦስትነቱ አራትነት የሌለበት፣ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምኜ፣ ከሦስቱ አንዱ ወልድ፣ ከሰማየ ሰማያት መውረዱን፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን፣ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን አምናለሁ፤ አስትምራለሁ፤ እመሰክራለሁ፣ መልሴንም፣ ‹አዎ! ኢየሱስ ፈጣሪ ነው› በሚል ርእስ በእግዚአብሔር አብ አነሳሽነት በእግዚአብሔር ወልድ ረዳትነት በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምሥጢር ገላጭነት እጀምራለሁ።»

«አንድ ፍጹም አምላክ ብቻ መኖሩን የሚያውጅ ሃይማኖት ቢኖር እስላም ብቻ ነው» የተባለው ፍጹም ሐሰት ነው፣ አንድ ብቸኛ አምላክ መኖሩን ከሁሉ አስቀድሞ ያወጀ የሙሴ ሕግ ‹የእስራኤል ሃይማኖት› ነው፤ «ስማ እስራኤል ሆይ! እግዚአብሔር አምላክህ አንድ ነው፣ አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም ኃይልህ ውደደው» ይላል (ዘዳግም 6፥4)።

www.ethiopianorthodox.org

# ሁለት መላምቶች

«ቢኖን በምትባል የደቡብ አፍሪቃ ከተማ አንድ ሰው ይኖራል፤ ይህ ሰው በሥነ መለኮት ትምህርት የነጠረ ዕውቀት የለውም፤ ሆኖም ግን ሙስሊሞችን ለማጥመቅ በክርስቶስ የተሾመ የፈጣሪ መላክተኛ እንደ ሆነ ደጋግሞ በመልፈፍ ራሱን ያታላላል፤ በጥብቅና ሙያ የሠለጠነው ይህ ሰው ቅንጣት የዓረብኛ ቃል ሳያውቅና ቁርአንን በአግባቡ ሳይረዳ በቃላት በመጫወትና የቅዱስ ቁርአንን አንቀጾች ያለቦታቸው በመጥቀስ በማወናበድ ረገድ በጣም የተካነ ነው፤ ሙስሊሞችን ኢየሱስ ‹ኢሳ› ፈጣሪ እንደሆነ ለማሳመን ይሻል፤ ይህ ዓይነቱ እምነት ደግሞ በአላህ ፍጹማዊ አንድነት ላይ እምነታቸውን ለአጸደቁ ሙስሊሞች ከቶውንም የማይዋጥላቸው ብቻ ሳይሆን በአላህ ሉዓላዊና ፍጹማዊ አንድነት ላይ ማሾፍ ሆኖ ይታያቸዋል፤ ይህ ብቻ አይደለም፤ በቅዱስ ቁርአን በግልፅ ሰፍሮ የሚገኘውን የአላህን ዓዋጅ የሚቃረን ጭምርም በመሆኑ ያወግዙታል፤ ሆኖም የዚህ መሰሪ ወንጌላዊ ሙስሊሞችን የማታለል ዘዴና ጥረቶች ሁሉ ያለ ጥርጥር ይከሽፋሉ፤ ምክንያቱም እውነት በአፈ ሙሌነት መቀልበስ የሚሞከር አይደለምና፤ ቅዱስ ቁርአን ይህን አስመልክቶ «እውነት መጣ፣ ውሸትም ይወገድ፤ እነሆ! ውሸት ተወጋጅ ነውና» ቁርአን ም ዕ.17፥81።

1. ኢየሱስ «አምላክ ነው...ስንል ወይም ‹እግዚአብሔር› እንደ ሆነ ስንከራከር ‹አብ ነው› ማለታችን አይደለም፤ የጌታን ባሕርይ ይጋራል ለማለት ነው፤

2. ኢየሱስ ከ «ፈጣሪ» ጋር ሁለንተናዊ የባሕርይ ተመሳሳይነት እንዳለው እርግጥ ነው፤ ሆኖም ግን ‹አብ አይደለም› ባጭሩ ሰውየው ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ባሕርይ የተላበሰና በሁለመናው የፈጣሪን ባሕርይ የሚያንጸባርቅ በመሆኑ በጌትነቱ ልንቀበለው እንደሚገባ ነው የሚሞግቱን» ብሏል።

<u>ሐተታ</u>፣ ሁለቱ የሰውየው መላምቶች ከሥነ መለኮት ትምህርት የተወሰዱ አይደሉም። ምክንያቱም የኩነታት ባሕርይ የላቸውም፤ ‹ኩነታት ማለት አብ ወልድን መንፈስ ቅዱስን አይሆንም፤ ወልድም



አብን መንፈስ ቅዱስን አይሆንም፣ መንፈስ ቅዱስም አብን ወልድን አይሆንም ማለት ነው›። ሰውየው ሊገልጠው የፈለገው ግን ኩነታትን ሳይሆን አብን ከፍ ወልድን ዝቅ አድርጎ ለማሳየት ስለ ሆነ ንስጥሮሳዊ ክህደት ነው።፣ ‹ዘእሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ› ወልድ በመለኮቱ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እኩል ነው፤ አይበላለጡም አይተናነሱም። የመጣጥፍ አዘጋጁ መጽሐፍ ቅዱስ እሱ እንዲናገር እንፍቀድለት ካለ በኋላ ኢየሱስን «አምላክ» «ፈጣሪ» «እግዚአብሔር» «ጌታ» እንደ ሆነ መስበክ በፈጣሪ ታላቅነት ላይ ማሾፍ ብቻ ሳይሆን ወደ ክህደት የመጨረሻ እርከን የሚያሽቀነጥር ነው፣ የሰው ልጆችንም የማመዛዘን ችሎታ የሚያረክስና የሚያኮስስ ስድብ ነው» ይልና! «ከዚህ በታች የሰፈሩት ጥቅሶች ሕጋዊና ይፋዊ ስርጭት ካለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው የተጠቀሱት፣ በዓቢይና በንዑስ ርዕሶቻችን ‹አምላክ» የሚለውን ቃል በጥቅስ ምልክት አስቀምጠናል፤ ይኸውም «ኢየሱስ አምላክ ነው» የሚለውን ጭፍን እምነት የማንቀበል መሆናችንን ለማመልከት ነው፤ ኢየሱስ በሚለው ቦታ አምላክ የሚለውን ቃል እየተካን ኢየሱስና አምላክ ተመሳሳይ መሆናቸውን ወይም ያለመሆናቸውን አስመስክር» ብሏል።

በፈጣሪው ላይ የሚያሾፍና በጭፍን የሚመራ፣ የፈጣሪውንም ስም የሚያረክስ አህመድ ዲዳት ብቻ ነው፤ እኛ ክርስቲያኖች ግን መነሻ መድረሻችንን መውጫ መግቢያችንን መሠማሪያችንና እረኛችንን ለይተን የምናውቅ የክርስቶስ መንጋዎች የክብሩ ወራሾች ምርጥ ሕዝቦች ነን። ወደ መጨረሻው የክህደት እርከን ተሸቀንጥራችሁ የሄዳችሁ እናንተና ተከታዮቻችሁ ናችሁ፣ «የእስራኤል ልጆች ሆይ፤ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን ይላል እግዚአብሔር (አሞጽ 9፥7)።

«ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ በሌላ በር የሚገባ እርሱ ሌባ ወንበዴ ነው፣ በበሩ የሚገባ ግን የበጎች እረኛ ነው፣ ለርእሱ በረኛው ይከፍትለታል፣ በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፣ በጎቹንም በየስማቸው ይጠራቸዋል፣ ያሰማራቸዋል፣ በፊታቸውም ይሄዳል፣ በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል፣ ከሌላው ግን ይሸሻሉ እንጂ አይከተሉትም፣ የሌላውን ድምፅ አያውቁምና...የበጎች በር እኔ ነኝ፣ በእኔ በኩል የሚገባ ይድናል፣ ይገባልም ይወጣልም መሠማሪያም ያገኛል፣ ሌባ ሊሰርቅ ሊያርድ ሊያጠፋ እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፣ እኔ



www.ethiopianorthodox.org

ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ መጣሁ፤ መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ መልካም እረኛ ስለ በጎቹ ሕይወቱን አሳልፎ ይሰጣል፤ እረኛ ያልሆነው በጎቹም የርሱ ያልሆኑ ምያተኛ ግን ተኩላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኩላውም ይነጥቃቸዋል፤ በጎችም ይበተናሉ፤ ምያተኛው ለበጎቹ ስለማይገደው ይሸሻል፤ መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ አብ እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ፤ በጎቼም ያውቁኛል፤ ሕይወቴን ስለ በጎቼ እሰጣለሁ፤ ከዚህ በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ አመጣቸው ዘንድ ሥልጣን አለኝ፤ እርሱም ለአንድ እረኛ አንድ መንጋ ይሆናሉ። ስለዚህ አብ ይወደኛል፤ ሕይወቴን እሰጣለሁ፤ ማንም ከእኔ አይወስዳትም፤ በፈቃድ እወስዳታለሁ፤ እወስዳት ዘንድ ሥልጣን አለኝ፤ ላኖራት ሥልጣን አለኝ፤ ላነሥትም ሥልጣን አለኝ»(ዮሐ.10፥1–18)።

ይህን ከዚህ በላይ የተነበበውን ኃይለ ቃል የተናገረ ቸሩ ጠባቂ የበጎች እረኛ የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከዚህ በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ አመጣቸው ዘንድ ሥልጣን አለኝ በማለት ጌትነቱን የሥልጣን ባለቤትነቱን አስታውቋል። ሕዝብን አሕዛብን አስጠንቅቋል፤ ጊዜው ደርሶ አንድ ቀን ዓለማችን የክርስትና በረት (ደሴት) እንደምትሆን አንጠራጠርም።

የመጽሐፍ ቅዱስን አንቀጾች ያለ ቦታቸው እየጠመዘዘና እንደ ፈለገው እየቀነጫጨበ ሌሎችን ለማሳሳት በተንኮል የተካነ እንደ አህመድ ዲዳት ያለ መልቲ በምድር ላይ የሚኖር አይመስለኝም። የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነትና ፈጣሪነት በመላምት የሚደረስበትና በይሆናል የሚተረጐሙት አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክ በመሆኑ ቅድመ ዓለም የነበረ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ ዓለምን የፈጠረ በኋላ ዘመን የሰው ልጆችን ለማዳን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው የሆነ ሥጋ የለበሰ የባሕርይ አምላክ ነው።

አህመድ ዲዳት በየጊዜው በክርስትና ሕይወት ላይ የሚሰነዝረው ነቀፋና የሚወረወረው የቃላት ፍላፃ የእኛን የተከታዮቹን ልብ ያደማል ያቆስላል እንጂ በክርስቶስ አምላክነት ላይ የሚያሳርፈው ጥቁር ነጥብ የለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ምርምርና ጥናቱ ተስፋ የቆረጠው ጸሐፊ በመጨረሻ «እውን ኢየሱስ ፈጣሪ ነው?» በሚል ርእስ አምላክ ተራበ፤



አምላክ ተጠማ አምላክ ደሰየ፣ አምላክ ተከዘ፣ አምላክ ተዋረደ...አቅመ ቢሱ አምላክ ደካማው አምላክ...በማለት እያፌዘ የጻፈውን መጣጥፍ አንብቤአለሁ። አዎ፣ ይህ ሁሉ የሥጋ ባሕርይ ነው፣ ከኃጢአት በስተቀር ክርስቶስ ያልሆነው ነገር የለምና አያሳፍረንም።

- በመንፈስ የተራቡት ለማጥገብ ተርቧል፤
- በመንፈስ የተጠሙትን ለማርካት ተጠምቷል፤
- በመንፈስ የደኸዩትን ለማበልጸግ ደኽይቷል፤
- በመንፈስ ያዘኑትንና የተከዙትን ለማረጋጋት አዝኗል ተክዟል፤
- በመንፈስ የተዋረዱትን ለማክበር ተዋርዷል፤
- ለድኩማን ኃይል ለመስጠት ኃይል የሌለው ደካማ መስሎ ታይቷል።

ይሁን እንጂ ይህን ሁሉ በራሱ ፈቃድ ያደረገው ስለ ሆነ የአምላክነት ባሕርዩን ዝቅ አያደርገውም።

አህመድ ዲዳት ቀደም ሲል በተከታታይ ባሳተማቸው የንጽጽር መጣጥፎች ሙስሊሞች ነቢያችን ነው ለሚሉት ለሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፈ ማስረጃ ያለው የመጨረሻው የአላህ መላክተኛ ነው በማለት ሸንጡን ገትሮ ተከራክሮለታል፤ ዕውቀቱን ገንዘቡና ጊዜውን ሠውቶለታል።

በአንፃሩ ደግሞ ትንቢት ተነግሮለት ሱባኤ ተቆጥሮለት ከሰማየ ሰማያት የወረደውን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደውን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ግን ጠበቃ ሆኖ ባደባባይ ተከራክሮታል፤ ሞግቶታል፣ እንደ ጲላጦስ ዳኛ ሆኖ ፈርዶበታል።

አህመድ ዲዳት የአቀራረብ ስልቱን እየለዋወጠ ቀደም ሲል ለጻፋቸው ሁለት መጣጥፎች ስለ ክርስቶስ አምላክነትና መድኃኒትነት የሰጠሁት መልስ በቂ መሆኑን ባምንበትም ይህን ግልጥ ክህደት አይቶና ሰምቶ ማለፍ ቤተክርስቲያኒቱን እንደ ደካማ ከማስገመቱም በላይ በመናፍቃኑም ዘንድ እንደ ታላቅ ድል ስለሚቈጠር ተገቢውን መልስ ሰጥቼበታለሁ። አቀራረቡም እንዳለፈው ከመልሱ በፊት የጽሑፉ አዘጋጅ ቀነጫጭቦ ያስፈራቸውን ጥቅሶች በማስቀደም ትክክለኛውን



www.ethiopianorthodox.org

ጥቅስ «ማስረጃ» እያከታተልሁ መልሱን አቅርቤዋለሁና በጥሞና ተከታተሉት።

«አስቀድሞ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፣ ሁሉ በርሱ ሆነ፣ ያለ እርሱ ምንም የሆነ ‹የተፈጠረ› የለም፣ ሕይወት በርሱ ነበረች...» ካለ በኋላ ዝቅ ብሎ፣ «ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ፣ ክብሩንም አየንለት» ይላል (ዮሐ.1፥1–14)።

«አብርሃም አባታችን እኔን ያይ ዘንድ ወደደ ‹ተመኘ› አይቶም ደስ አለው» ቢላቸው አይሁድም «ገና አምሳ ዓመት አልሞላህ እንዴት አብ ረሃምን አየሁ ትላለህ?» አሉት። እርሱም፣ «አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ ቢላቸው ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ» ይላል (ዮሐ.8፥56–59)።

እንግዲህ አውቆ የተሸሸገ ቢጠሩት አይሰማም እንደሚባለው ለሚሰማ እንጂ ለማይሰማ 99 ማስረጃ ቢደረድሩለት ዋጋ አይኖረውም። ሆኖም ይህን የመጨረሻ የክህደት መላምት በማጋለጥ ዕርቃነ ሥጋውን ለማስቀረት ከዚህም ከዚያም እየቀነጨበ የጠቀሳቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መነሻና መድረሻ እያብራራሁ የማርያም ልጅ መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ፈጣሪ የሁሉ ጌታ መሆኑን ከዚህ በረት ላልሆኑት ማለት ከክርስትናው ዓለም ውጭ ለሆኑት ሁሉ እሰብካለሁ፤ አስተምራለሁ፣ እመሰክራለሁ። በክርስቶስ አምላክነት ላይ የሚያሾፈውንና ስሙን ከንቱ የሚያደርገውን መናፍቅ ሳይቀሥፈው አይተወውም፤ «የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም ከንቱ አታድርገው፣ እግዚአብሔር ስሙን ከንቱ ያደረገውን ሳይቀሥፈው አይተውምና» (ዘጸአት 20፥7)።

## የ«አምላክ» ልደት!

አምላክ ከዳዊት ዘር መፈጠሩን ለማመልከት «በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ» ይላል (ሮሜ.1፥3–4)።

«ነቢይ ነበረና ስለ አወቀ እግዚአብሔር መሐላ እንደ ማለለት ከወገቡ ፍሬ ክርስቶስን እንዲያስነሣ እንደ ሥጋ በዙፋኑ ይቀመጥ ዘንድ» (የሐዋ.2፥30)።



<u>ሐተታ</u>፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም በሥጋ የተወለደ እንጂ የተፈጠረ አይደለም።

ተፈጠረ የሚባል በእናትና በአባት ግንኙነት ሲወለድ ነው፣ ጸሐፊው «ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ» የሚለውን ቀንጭቦ ወስዶ «የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ተገለጠ» የሚለውን ቆርጦ አስቀርቶታል፣ ጸሐፊው ዋሾ ቢሆን የእግዚአብሔር ቃል አይዋሽም፣ «እርሱ ታላቅ ይሆናል፣ የልዑል ልጅም ይባላል፣ እግዚአብሔር አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ወገን ላይ ለዘላለም ይነግሣል፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም» (ሉቃ.1፥32)።

«የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ፣ ከሴት የተወለደውን ከአሪት በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ» (ገላ.4፥4)።

## የ«አምላክ» የዘር ሐረግ!

«የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ» (ማቴ.1፥1)።

<u>ሐተታ</u>፣ የኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ ምድራዊ ብቻ አይደለም፤ ሙስሊሙ ጸሐፊ አያውቀውም እንጂ ሰማያዊም የዘር ሐረግ አለው፤ ዓለም ሳይፈጠር ያለ እናት በአባት ብቻ መወለዱ ‹ቀዳማዊ ልደቱ› ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ መወለዱ ‹ደኃራዊ ልደቱ› ነው፤ ቀዳማዊ ልደቱ በዚህ ጊዜ በዚህ ስፍራ ነው አይባልም፤ ምድራዊ ልደቱ ግን በዳዊት አገር በዳዊት ከተማ በቤተ ልሔም ሲሆን ዘመኑም የዓመተ ምሕረት መጀመሪያ ነው። ከዚያ በፊት የነበረው ዘመን ግን ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ ይባላል፤ ማቴዎስ ከዳዊት ጀምሮ ቁልቁል የቈጠረውን ትውልድ ሉቃስ ደግሞ ከዮሴፍ ጀምሮ ወደ ላይ ይቈጥርና በመጨረሻው ላይ ‹የአዳም ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ» ይላል፤ የልደቱ ማስረጃ ነው፤ ከዚህም ሌላ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በራሱ ላይ ወርዶ ሲያርፍበት አብ በደመና ላይ ሆኖ የምወደው ልጄ ይህ ነው፣ እርሱን ስሙት» በማለት የባሕርይ ልጅነቱን አስመስከሯል።



www.ethiopianorthodox.org

## የ«አምላክ» ፆታ!

«ስምንት ቀን ሲሞላው ሕፃኑን ሊገርዙት ወሰዱት፤ አስቀድሞ ሳይፀነስ ስሙ በመልአኩ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ» (ሉቃ.2፥21)።

<u>ሐተታ</u>፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ እንደ መሆኑ መጠን የኦሪትን ሕግ እየፈጸመ ቀስ በቀስ አድጓል፤ ሆኖም ወደ ቤተ ግርዘት ይሂድ እንጂ የሰው እጅ አልተጠበበበትም፣ ‹ማለት አልነካውም› በመንፈስ ቅዱስ ተገርዞ ተገኝቷል (ዘሌዋ? 12፥3፤ ሉቃ.2፥21)።

## ማርያም «አምላክን» ስለ መፀነሷና መውለዷ

«እንዴት ነው ማርያም አምላክን አርግዛ የወለደችው? ማርያም እንደ ማንኛዋም ሴት አርግዛ በቀኗ እንደ ወለደችው ለማመልከት «በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ፣ የበኩር ልጇንም ወለደች» (ሉቃ.2፥6)።

ይህም ማለት ማርያም ተፈጥሯዊ የፅንስ ወራትን እንደ ማንኛዋም ሴት መፈጸሟን እንረዳለን፤ የአወላለዷም ሁኔታ በማናቸውም መለኪያ ቢሆን ከመሰል ሴቶች የተለየ አልነበረም።፣ «እርሷም ፀንሳ ነበር፣ ምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጨንቃ ጮኸች» በማለት ራእይ12፥2 ዋቢ ጠቅሷል።

<u>ሐተታ</u>፣ መቸም ጸሐፊው ከተመቸውና ካገኘ የማይሰበስበው እንጨት የማይለኩሰው እሳት የለም። ቅድስት ድንግል ማርያም ክርስቶስን ስትወልደው ሴቶች የሚሰማቸው ሳይሰማት እርሱንም ሕፃናትን የሚሰማቸው ሳይሰማው ነው የወለደችው፤ ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ ሄሮድስ ሊገድለው ስለ ፈለገ እናቱ ድንግል ማርያምና ዮሴፍ ይዘውት ወደ ግብፅ ተሰደዱ፤ ጸሐፊው ዋቢ አድርጎ በጠቀሰው ራእይ 12፥2 ላይ አውሬው ይችን ሴት ከኋላዋ ተከተላት፣ ከወደ ኋላዋም ላይ ፈሳሽ ውኃ ለቀቀባት ምድርም አፍዋን ከፍታ ፈሳሹን ውኃ መጠጠችላት፣ ማለት በአውሬ የተመሰለው ንጉሡ ሄሮድስ እናቱና ሕፃኑ ወደ ግብፅ መሰደዳቸውን ስለ አወቀ አሳድዶ የሚያጠፋቸው ብዙ ሠራዊት አከታትሎ ላከ፣ ይሁን እንጂ በየመንገዱ ወድቆ ወድቆ ቀርቷል፣ ለርሷም ኃይል ተሰጣት ማለት የታቀፈችው ሕፃን ሰወራት፣



ተጨነቀች ማለት ሄሮድስ ልጇን ይገድልብኛል ብላ አሰበች ተጨነቀች ማለት ነው።

የአወላለዷ ሁኔታ በማንኛውም መለኪያ ቢሆን ከመሰል ሴቶች የተለየ አልነበረም ብሏል፣ የጸሐፊው ነገረ ዘርቅ ነው፣ ሌላው ቀርቶ ቁርአንን የሚቃረን ነው፣ «ማርያም ሆይ! አላህ በእርግጥ መረጠሽ፣ አነጻሽም፤ በዓለማት ሴቶች ላይ መረጠሽ» ይላል፣ (ቁርአን ምዕ.3፥42)። «መልአኩም ወደርሷ ገብቶ ጸጋን የተመላሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ፣ እግዚአብሔር ካንች ጋር ነውና፣ ከሴቶች ሁሉ አንች የተባረክሽ ነሽ፣ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው» (ሉቃ.1፥28)።

እንግዲህ እነዚህ ሁለት የሃይማኖት መመሪያዎች ‹ቁርአንና ሐዲስ ኪዳን› እንዳስረዱት ቅድስት ንጽሕት ድንግል ማርያም ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደችው መሆኗ እየታወቀ አወላለዷ ከሴቶች የተለየ አልነበረም እንዴት ይባላል? የትኛዋ ሴት ናት በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች? እጅግ በጣም ያሳዝናል፣ ጸሐፊው ይህን ኢሞራላዊ ቃላት ሲሰነዝር ማንን የጎዳሁ ይመስለው ይሆን? የሚጎዳው ራሱን ነው፤ «ለዚህ ሰው ወዮለት፣ ያ ሰው ባልተወለደ ይሻለው ነበር» (ማቴ.26፥24)።

## «አምላክ» የሴት ጡት ጠብቷል!

«ይህንም ሲናገር ከሕዝብ አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፡- የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው አለችው» (ሉቃ.11፥27)።

<u>ሐተታ</u>፣ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነው፤ ፍጹም አምላክ ነኝ ብሎ ዕለቱን ሊደግ አላለም፣ በዝናም አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ ፍጥረቱን ሁሉ የሚመግብ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ያንዲት ቅድስት ንጽሕት ልጃገረድ ጡት እየጠባ ቀስ በቀስ አድጓል። «ሕፃኑም አደገ፣ በመንፈስም ፀና፣ ጥበብም ሞልቶበት ነበር፣ የእግዚአብሔር ጸጋ በርሱ ላይ ነበረችበት» (ሉቃ.2፥40)።



www.ethiopianorthodox.org

## የ«አምላክ» የትውልድ መንደር!

«ኢየሱስም በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን በይሁዳ ዕጣ በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ» (ማቴ.2፥1)።

<u>ሐተታ</u>፣ ክርስቶስ የተወለደባት ከተማ ቤተልሔም ቀደም ሲል ትንቢት ተነግሮላታል። «የይሁድ ምድር የምትሆኝ አንች ቤተልሔም ይሁዳ ነገሥታት ከነገሡባቸው አገሮች ብትበልጭ እንጂ አታንሽም» ሚክ.5፥2)።

## የ«አምላክ» ሙያ!

«ይህ የእንጨት ሀራቢው ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለችም? ወንድሞቹስ ያዕቆብ ዩሳም ይሁዳም ስምዖንም አይደሉምን?» (ማር.6፥3፤ ማቴ.13፥55)።

<u>ሐተታ</u>፣ ለክርስቶስ የሥጋ ወንድሞች የሉትም፣ አብረውት የደጉትን በስሙ ያመኑትን ወንድሞቼ ይላቸዋል።« እናቱና ወንድሞቹ ነውጭ መጥተው ሊገናኙት ላኩበት፣ ሰዎች ዙሪያውን ተቀምጠው ነበር። እነሆ! እናትህና ወንድሞችህ ከውጭ ቆመው ይፈልጉሃል አሉት፣ እርሱም እናቴ ማናት? ወንድሞቼስ? በዙሪያው ወደ አሉት ሰዎች እየተመለከተ እናቴም ወንድሞቼም የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ ነው አላቸው» (ማር.3፥31–35)።

## የ«አምላክ» መጓጓዣ ዘዴ!

«ለጽዮን ልጅ እነሆ ንጉሥሽ የዋህ በአህያ ላይ ባህያይቱ ግልገል በውርንጭላይቱ ተቀምጦ ወደ አንች ይመጣል በሏት» (ማቴ.21፥5፤ ዮሐ.12፥15)።

<u>ሐተታ</u>፣ ትንቢታዊ ማስረጃ ነው፣ «አንች የጽዮን ልጅ እጅግ ደስ ይበልሽ፣ አንችም የኢየሩሳሌም ልጅ እልል በይ፣ እነሆ! ንጉሥሽ ይመጣል ጻድቅ መድኃኒትም እርሱ ነው፣ ድኃ ሆኖ በአህያም ተቀምጦ በአህያይቱ ግልገል በውርንጭላይቱ ላይ» (ዘካ.9፥9)።



## የ«አምላክ» ምግብና አስካሪ መጠጥ

«የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጣ፤ እነሆ በላተኛና ጠጅ ጠጭ የቀራጮችና የኃጢአተኞች ወዳጅ አሉት» (ማቴ.11፥19፤ ሉቃ.7፥34)።

<u>ሐተታ</u>፣ የጽሑፉ አቅራቢ ቆርጦ ያስቀረው ቁጥር 18 «ዮሐንስ ግን ሳይበላ ሳይጠጣ ቢመጣ ጋኔን አለበት አሉት» ይላል። ታዲያ! አይሁድ የሚበላውን በላተኛ የማይበላውን ጾመኛ ካሉት ምን ዓይነት መምህር ነበር የሚፈልጉት? አንተስ ሙስሊሙ ጸሐፊ የትኛውን ትመርጣለህ? በላተኛውን? ወይስ የማይበላውን?

## የ«አምላክ» ድህነት!

«ኢየሱስ ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይ ወፎች መጠለያ አላቸው፣ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም አለው» (ማቴ.8፥20)።

<u>ሐተታና ማስረጃ</u>፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 33 ዓመት ከሦስት ወር በዚህ ዓለም ሲቆይ ቤት ንብረት አልነበረውም፣ ቀን በምኵራብ ሲያስተምር ውሎ ሌሊት ደብረ ዘይት በሚባል ተራራ ያድር ነበር (ሉቃ.21፥38)።

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ ሰማይ ዙፋኔ ነው፣ ምድርም የእግሮቼ መረገጫ ናት፣ ምን ቤት ነው የምትሠሩልኝ? የማርፍበትስ ምን ስፍራ ነው?» (ኢሳ.66፥1)።

## የ«አምላክ» ቁሳቁሶች!

«የጫማውን ጠፍር...» ማቴ.3፥11፤ «ጭፍሮችም ኢየሱስን በሰቀሉት ጊዜ ልብሶቹን ወስደው ለእያንዳንዱ ጭፍራ አራት ክፍል አደረጉት፤ ቀሚሱ ደግሞ ያልተሰፋ ነበር፤ ከላይ ጀምሮ እስከ ታች አልቀደዱትም፤ ዕጣ ተጣጣሉበት እንጂ» (ዮሐ.19፥23)።

<u>ሐተታ</u>፣ ጸሐፊው ቆራጣ ጠፍር አድርጎ ያስቀረው ጥቅስ ሙሉ ቃል «ዮሐንስም መልሶ አላቸው፣ እኔስ በውኃ አጠምቃችኋለሁ ከእኔ የሚበረታ ግን ይመጣል፣ የጫማውን ማሰሪያ እፈታ ዘንድ የማይቻለኝ እርሱ ያጠምቃችኋል፣ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም» ይላል(ማቴ.3፩1)።

www.ethiopianorthodox.org

«ልብሶቼን ለራሳቸው ተካፈሉ፣ በልብሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ» በማለት የተናገረው ቀደም ሲል ነቢዩ ዳዊት የተናገረው ትንቢት ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ነው፣ (መዝ.22፥18)።

## አማኝ ይሁዳዊ «አምላክ»

«እጅግ ማለዳም ሌሊት ተነሣ፤ ወደ ምድረ በዳም ሄዶ ይጸልይ ነበር» (ማር.1፥35)።

<u>ሐተታ</u>፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው፣ በፍጹም ሰውነቱ ይጸልይና ለደቀ መዛሙርቱም አባታችን ሆይ! በሉኝ እያለ ሥርዓተ ጸሎት ያስተምራቸው ነበር፣ በፍጹም አምላክነቱ ደግሞ ልዩ ልዩ ተአምራት ያደርግ ነበር፣ ማለት ድውይ ይፈውስ፣ ሙት ያስነሣ ነበር (ማር.1፥30–35)።

## መልካም ዜጋና ለቄሳርም ታማኝ «አምላክ»!

«የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አስረክቡ አላቸው» (ማቴ.22፥21)።

<u>ሐተታ</u>፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው እንደ መሆኑ መጠን በሰውነቱ ለቄሣር ‹ለዚህ ዓለም ገዥዎች› ግብር መስጠት እንዲገባ ፈቅዷል። ፍጹም አምላክ እንደ መሆኑ መጠን ደግሞ በተወለደ ጊዜ ሰብአ ሰገልን አስገብሯል። «ወደ ቤተልሔም መጡ፣ ሕፃኑንም ከእናቱ ከማሪያም ጋር አገኙት፣ ወድቀው ሰገዱለት፣ ሣጥናቸውንም ከፈቱ፣ የእጅ መንሻ ወርቅ ዕጣንና ከርቤ ገበሩለት (ማቴ.1፥35)።

## ግብር ከፋይ «አምላክ»!

«ወደ ቅፍርናሆም በመጡ ጊዜ ግብር የሚቀበሉ ሰዎች ወደ ጴጥሮስ ሄደው መምህራችሁ ሁለት ዲናር አይገብርምን? አሉት፤ አዎ፤ ይገብራል አሉ» (ማቴ.17፥25)።

<u>ሐተታ</u>፣ ጸሐፊው ቀንጭቦ የጻፈው ጥቅስ ሙሉ ቃል «ጴጥሮስም ወደ ቤት በገባ ጊዜ ኢየሱስ አስቀድሞ ሲሞን ሆይ ምን ይመስልሃል? የምድር ነገሥታት ከማን ግብር ዕዳስ ይቀበላሉ? ከልጆቻቸው ወይስ ከሌሎች? አለው፣ ጴጥሮስም ከሌሎች ነው አለው፣ ኢየሱስም እንግዲያውስ ልጆቻቸው ጌቶች ‹ነፃ› ናቸው፣ ነገር ግን መሰናክል እንዳንሆንባቸው ወደ ባሕር ሂድና መቅጥን ጣል፣ በፊት የወጣውን ዓሣ ውሰድና አፉን ከፈት፣ በርሱም አራት ድራም ታገኛለህ፤ ውሰድና ስለ እኔና ስለ እናንተ ስጣቸው» ይላል።

ክርስቶስ አምላክ እንደ መሆኑ መጠን ዓሣን አስገበረ፣ ሰው እንደ መሆኑ ደግሞ ከተማሪዎቹ ጋር ግብር ከፈለ።

## የ«አምላክ» ቤተሰብ!

«አምላክ የዮሴፍ ልጅ ነበር፤ ፊልጶስ ናትናኤልን አግኝቶ ሙሴ በኦሪት ነቢያትም ስለርሱ የጻፉለትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስን አገኘው አለው» (ዮሐ.1፥46)።

<u>ሐተታ</u>፣ ክርስቶስ የዮሴፍ ቤተሰብ ሆኖ ማደጉ አይካድም። ነገር ግን ፊልጶስ እንዳለው ዮሴፍ የኢየሱስ አባት አልነበረም። ኢየሱስ ክርስቶስማ በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና መወለዱን ቅዱሳት መጻሕፍት ቁርአን ሳይቀር ያረጋገጡት ሐቅ ነው፣ «እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች» (ማቴ.1፥18)።

## የ«አምላክ» ወንድሞች!

«ወደ ገዛ አገሩ መጥቶ እስኪገረሙ ድረስ በምኵራባቸው ያስተምራቸው ነበር፤ ከወዴት ይህ ጥበብ ለርሱ ተሰጠው? ይህ ኃይልስ? ይህ የአንጢት ፀራቢው ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለችምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብ ዮሳም ሲሞንም ይሁዳም አይደሉምን? እኅቶቹስ ሁሉ በእኛ ዘንድ ያሉ አይደሉምን?» (ማቴ.13፥54)።

<u>ሐተታ</u>፣ ይህ ሁሉ የጠላቶቹ የአይሁድ ወሬ ነው። እናቱ ድንግል ማርያም ምን ጊዜም ቅድስት ንጽሕት ናት። ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስም የባሕርይ አምላክ ነው፤ «የበኵር ልጇን እስክትወልድ ድረስ ዮሴፍ አላወቃትም» (ማቴ.1፥25)።


www.ethiopianorthodox.org

የአምላክ መንፈሳዊ ዕድገት፤ «ሕፃኑ ግን አደገ፣ በመንፈስም ጸና፣ ጥበብ ተሞልቶበት የእግዚአብሔርም ጸጋ ከርሱ ጋር ነበር» (ሉቃ.2፥40)።

የአምላክ አካላዊ አእምሮአዊና ባሕርያዊ ዕድገት፤ «ኢየሱስም ደግሞ በጥበብ በቁመትና በሞገስ በኢግዚአብሔርና በሰው ዘንድ ያድግ ነበር» (ሉቃ.2፥52)

«ወላጆቹ በየዓመቱ ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር፤ በዚህ ጊዜ (አምላክ) ኢየሱስ 12 ዓመት ሞልቶት ነበር፤ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ሲሆነው እንደ በዓሉ ሥርዓት ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ» (ሉቃ.2፥41–42)።

## አቅመ ቢሱ «አምላክ»!

«እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ፤ ፍርዴም ቅን ነው፤ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና» (ዮሐ.5፥30)።

<u>ሐተታ</u>፤ ክርስቶስ አቅመ ቢስ አይባልም፤ እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ፤ አብና ወልድ ‹አባትና ልጅ› በፈቃድ በሥራና በባሕርይ አንድ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነው እንጂ አብ ከወልድ ይበልጣል ወልድም ከአብ ያንሳል ማለት አይደለም፤ «እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ.10፥30)። «...እኔ ነኝ የሕይወት እንጀራ፤ ወደኔ የሚመጣ አይራብም፤ የሚያምንብኝም ለዘላለም አይጠማም» (ዮሐ.6፥35)። «እኔ መንገድ ነኝ፤ እውነትም ሕይወትም፤ አንድም ወደ አብ የሚመጣ የለም፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በስተቀር፤...በእኔ እመኑ፤ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ፤ ወይም ስለ ሥራዩ በእኔ እመኑ» (ዮሐ.14፥6–11)።

## «አምላክ» ስለ ምፅዓት አያውቅም!!

«ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ግን የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም» (ማር.13፥32)።

<u>ሐተታ</u>፤ አብ የሚያውቀውን ወልድ አያውቅም ማለት አይደለም፤ ያለ አዋቂ ሥጋን እንደ ለበሰ ለማስረዳት ነው፤ «አብ በማንም አይፈርድምና፤ ነገር ግን ፍርዱን ሁሉ ለልጁ ሰጠው» (ዮሐ.5፥22)።



«የሰው ልጅ በምስጋናው በመጣ ጊዜ ቅዱሳን መላእክትም ከርሱ ጋር ያን ጊዜ በምስጋናው ዙፋን ይቀመጣሉ፤ አሕዛብ ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እርስ በርሳቸውም ይለያቸዋል፤ ጠባቂ በጎችን ከፍየሎች እንዲለይ፤ በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማል፤ ያን ጊዜ ንጉሡ በቀኙ ያሉትን ይላቸዋል፤ የአባቴ ቡሩካን ኑ ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ትወርሱ ዘንደ፤ ተርቤ አብልታችሁኛልና፤ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፤ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፤ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፤ ታስሬ አስፈትታችሁኛልና፤ ...ከዚህ በኋላ ደግሞ በግራው ያሉትን ከእኔ ራቁ እናንተ ርጉማን፤ ለሰይጣንና ለመላከተኞቹ ወደ ተዘጋጀው የዘላለም እሳት ይላቸዋል፤ (ማቴ.25፥41)።

## «አምላክ» ወቅት መለየት አቃተው!!

«በማግስቱ ከቢታንያ ሲወጡ ተራበ፤ ቅጠል ያለበት በለስ በሩቁ አይቶ ምናልባት አንዳች ይገኝባት እንደሆነ ብሎ ወደርሷ መጣ፤ ነገር ግን የበለስ ወራት አልነበረምና ከቅጠል በቀር ምንም አላገኘባትም» (ማር.11፥12)።

<u>ሐተታ</u>፤ በአምስት እንጀራ በሁለት ዓሣ እልፍ አዕላፋት ሕዝብ የመገበ ጌታ ምግብ አስፈልጎት ወቅቱ ተሰውሮት አይደለም፤ ምሳሌ ነው፤ በለስ የተባለች እስራኤል ናት፤ አምላክ ወልደ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግ ሊሠራላት ምግባር ሃይማኖት ሊያስተምራት ወደ እስራኤል መጣ፤ እስራኤል ግን አልተቀበላቸውም፤ በሌላ ክፍል ረገማት ደረቀች» ይላል፤ እስራኤል ክርስቶስን ከሰቀለች በኋላ በጥጦስ ዘመነ መንግሥት በ70 ዘመን ጠፋች፤ እስራኤላውያን በዓለም ላይ ተበተኑ፤ የክርስቶስ ደም ብቀላ በዚህ ብቻ አላበቃም፤ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት 6000000 ያህል አይሁዳውያን በጭካኔ ተጨፍጭፈው አልቀዋል፤ ‹ጲላጦስም...ውኃ አስመጥቶ እኔ ከዚህ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ ሲል እጁን ሲታጠብ ሕዝቡ ‹ሊቃነ ካህናቱ› ደሙ በእኛና በልጅ ልጆቻችን ላይ ይሁን ሲሉ» ኃላፊነቱን ወስደዋል (ማቴ.27፥24–25)።

www.ethiopianorthodox.org

## «አምላክ» አልተማረም!!

«አሁንም በበዓሉ እኩሌታ ወደ መቅደስ ወጥቶ ያስተምር ነበር፤ አይሁድም ይህ ሰው ሳይማር መጻሕፍትን እንዴት ያውቃል?» በማለት ያደንቁ ነበር (ዮሐ.7፥14)።

<u>ሐተታ</u>፤ ለፍጥረቱ ሁሉ ዕውቀትን የሚያድል የዕውቀት ባለቤት ጌታ እንዴት አልተማረም? አይሁድ የሚያዩት በሰውነቱ ብቻ ነበር፤ የዕውቀት ባለቤትነቱ አልተከሰተላቸውም፤ በወቅቱ በነበረው ትምህርት ቤት ገብቶ ሳይማር በምኵራባቸው እየገባ የነቢያትን መጻሕፍት አንብቦ ሲተረጕምና ሲያስረዳ የአንደበቱን ቅልጥፍና የንግግሩን ለዛ አይተው አድናቆታቸውን ይገልጡ ነበር (ሉቃ.4፥16–12)።

## «አምላክ» ከልምድ ዕውቀትን ገብይቷል

«ምንም ልጅ ቢሆን ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ» (ዕብ.5፥8)።

<u>ሐተታ</u>፤ አምላክ ‹ኢየሱስ› ኃጢአቱን ተናዘዘ ንስሐ ገባ አይባልም፤ ድፍረት የተሞላበት ብልግና ነው። በዚህስ አይሁድ ጠላቶቹም አላሙትም፤ በሕይወት ታሪኩም አልተጻፈም፤ ሐዲስ ኪዳን እንደሚያስረዳው ሕዝቡ ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ በዮሐንስ እጅ ተጠምቀዋል እንጂ ክርስቶስ ማንንም አላጠመቀም፤ ክርስቶስ የተጠመቀው ኃጢአት ኖሮበት አይደለም፤ የጥምቀት ጀማሪ በመሆን ዳግም ልጅችን (ጥምቀትን) ለማስተማር ነው። «ማንም ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባ ዘንድ አይቻልም» (ዮሐ.3፥5)።

## «አምላክ» በሰይጣን ተፈተነ!

አምላክ ለአርባ ቀን በሰይጣን ተፈተነ፤ «ከዚያ በኋላ ኢየሱስን መንፈስ ወደ ምድረ በዳ አወጣው፤ ከዲያቢሎስ ይፈተን ዘንድ፤ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ተራበ» (ማቴ.4፥1–2)።

<u>ሐተታ</u>፤ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደ መሆኑ መጠን ዕውቀት የባሕርዩ ነው፤ ሰው እንደ መሆኑ ደግሞ ስለ ትሕትና ለእናቱና ለዘመዶቹ እየታዘዘ አደገ። «ከርሳቸውም ጋር ወደ ናዝሬት መጣ፤ ለእርሳቸውም



ይታዘዝ ነበር፤ እናቱም ይህን ሁሉ ነገር በልቧ ትጠብቀው ነበረች» (ሉቃ.2፥51)።

## የ«አምላክ» ተልዕኮ!

«አምላክ» ኃጢአቱን ተናዘዘ፤ ንስሐም ገባ»፤ «ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ» (ማቴ.3፥13)። «ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከርሱ ይጠመቁ ነበር» (ማቴ.3፥6)።

«አምላክ ሳያሰልስ በሰይጣን ተፈተነ፤ ሰይጣንም ፈተናውን ሁሉ ከፈጸመ በኋላ እስከ ጊዜው ከርሱ ተለየ»(ሉቃስ 4፥13)።

«አምላክ እንደ ኃጢአተኞች ሁሉ በሁሉም ይፈተናል»፤ «ከብቻዋ ከኃጢአት በስተቀር በሁሉም ነገር እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ» (ዕብ.4፥15)።

«ማንም ሲፈተን እግዚአብሔር ፈተነኝ አይበል፤ እግዚአብሔር ማንንም በክፉ አይፈትንምና፤ ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል» (ያዕ.1፥13–14)።

<u>ሐተታ</u>፤ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት እህል ውኃ ሳይቀምስ ሊቆይ የሚችል ፍጡር አለን? በፍጡር ደረጃ የማይሞከር ነው፤ ክርስቶስ ግን በአምላካዊ ባሕርዩ ሊቆይ ችሏል፤ ሰው እንደ መሆኑ መጠን ደግሞ ተራበ፤ በዚህ ጊዜ ፈታኙ ሦስት ድንጋይ በቀዳዳ ስልቻ ይዞ «የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ እነዚህ ድንጋዮች ዳቦ ይሆኑ ዘንድ እዘዝ አለው፤ እርሱም ሰው በእንጀራ ብቻ አይድንም፤ በእግዚአብሔር ቃል ጭምር እንጂ» (ማቴ.4፥3–4)።

የክርስቶስ ፈተና ከሰዎች ፈተና ፍጹም የተለየ ነው፤ የሰው ልጆች የሚፈተኑት ጥቅማቸውንና ክብራቸውን ሲያሳድዱ ነው፤ ክርስቶስ ግን ሥጋ በመልበሱ ብቻ ልዩ ልዩ ፈተና ደርሶበታል፤ ታላቁና የመጨረሻው ፈተና በመስቀል ላይ የደረሰበት ግፍ ነው፤ ሉቃስ እስከ ጊዜው ማለቱ፤ ሰይጣን በይሁዳ ላይ አድሮ፤ በዕለተ ዓርብ እስቲያሰቅለው ድረስ አይመለስበትም ማለቱ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

## «አምላክ» ኃጥአንን ሊያነፃ አልመጣም!!

«ብቻውን በሆነ ጊዜ በዙሪያው የነበሩት ከአሥራ ሁለቱ ጋር ስለ ምሳሌው ጠየቁት፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥጢር ታውቁ ዘንድ ለእናንተ ተሰጥቷችኋል፣ በውጭ ላሉት ግን ሁሉ ነገር በምሳሌ ይሆንላቸዋል፣ ማየትን እያዩ እንዳይመለከቱ፣ መስማትን እየሰሙ እንዳያስተውሉ እንዳ ይመለሱና ኃጢአታቸውም እንዳይሰራይላቸው» (ማር.4፥10–12)።

ሐተታ፣ ይህ የክርስቶስ ትምህርት አይደለም፣ የኢሳይያስ ትንቢት ነው፣ ጸሐፊው ትምህርቱንና ትንቢቱን ለይቶ ስለማያውቀው ነው፣ አምላክ ወደዚህ ዓለም የመጣውና ሰው የሆነው ኃጢአተኞችን ለማዳን እንጂ ለጻድቃን አይደለም፣ ትንቢቱን ለእስራኤል ሕዝብ የተናገረው ኢሳይያስ ነው፣ የክርስቶስ ትምህርት ግን «በቤቱም ለምሳ ተቀምጦ ሳለ ብዙ ቀራጮችና ኃጢአተኞች መጡ፣ ለምሳም ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብረው ተቀመጡ፣ ፈሪሳውያንም አይተው ለምን መምህራችሁ ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ይበላል? አሏቸው፣ ኢየሱስም ይህን በሰማ ጊዜ አላቸው፣ ባለመድኃኒትን በሽተኞች እንጂ ጤነኞች አይፈልጉትም፣ ከመሥዋዕት ይልቅ ምህረትን እወዳለሁ ያለውን ዕውቁ፣ ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ ልጠራ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም» (ማቴ.9፥10–13)።

## ዘረኛ «አምላክ»

«ነገደ ይሁዳ ‹አምላክ› እነሆ ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ» (ራእ.5፥5)። ለአይሁድ ብቻ የመጣው «አምላክ» እርሱም መልሶ ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም አለ» (ማቴ.15፥24)።

ሐተታ፣ ክርስቶስ ለአይሁድ ብቻ የመጣ አምላክ አይደለም፣ ከእስራኤል ለጠፉት በጎች ነው የተላከው ማለቱ እምቢተኝነታቸውን ለማጋለጥ ነው፣ ሌላም ምክንያት ነበረው፣ ቀደም ሲል ያቀረበላትን ጥያቄ አስወድዶ አስፈቅዶና አሳምኖ ለመፈጸም ነው፣ አንዲት የከነዓን ሴት ልጇን አድንልኝ ብላ ብትጠይቀው እኔ የመጣሁ በቅድሚያ ትንቢት ለተነገረላቸው ሱባኤ ለተቆጠረባቸው ለቤተ እስራኤል ነው አላት፣ እርሷ ግን ሳትፈራ ሳታፍር በፊቱ እየሰገደች አቤቱ እርዳኝ ልጄን አድንልኝ ስትል መላልሳ ተማጸነችው፣ እርሱም የልጆችን እንጀራ ነጥቆ ለውሾች መስጠት አግባብ አይደለም ቢላት አዎ፣ አቤቱ ውሾችም እኮ ከጌቶቻቸው ማዕድ የወደቀውን ፍርፋሪ ይመገባሉ አለችው፣ በዚህ ጊዜ ክርስቶስ አንች ሴት ሃይማኖትሽ ታላቅ ነው፣ እንደ ወደድሽ ይደረግልሽ አላት፣ በዚያ ሰዓት ልጇ ፈጥና ዳነች። ክርስቶስም የፈለገው ይህን ነው፤ አስወድዶና አስፈቅዶ ለማድረግ ነው፣ ምሳሌ መስሎ ቢመልስላት እርሷም ትሕትና በተላበሰ አንደበት ምሳሌ መስላ መለሰችለት፣ ክርስቶስም በምሳሌዋ ቅልጥፍናና የሃይማኖቷን ጥንካሬ እያደነቀ ልጇን አዳነላት፣ ይህ ዘረኛነት አይደለም፣ የማስተማር ዘዴ ነው፣ (ማቴ.15፥22–28)።

## የ«አምላክ» መንግሥት

«በያዕቆብ ቤት ላይም ለዘላለም ይነግሣል፣ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም» (ሉቃ.1፥33)።

ሐተታ፣ የክርስቶስ መንግሥት ምድራዊና ያዕቆባዊ አይደለም፣ ሰማያዊና ዘላለማዊ ነው። «ጲላጦስም አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን? ቢለው ክርስቶስም ይህን አንተ ከልብህ አስበህ ተናገርህ? ወይስ ሌሎች ነገሩህ ቢለው፣ ጲላጦስም እኔ አይሁዳዊ አይደለሁም፣ ወገኖችህ ካህናት ወደኔ አመጡህ፣ ምን አድርገሃል አለው፣ ክርስቶስም መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፣ መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን ለአይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ መላእክት በተዋጉልኝ ነበር፣ ነገር ግን መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም አለው» (ዮሐ.18፥33–36)።

## የ«አምላክ» የማዕርግ ስሞች

«የአይሁድ ንጉሥ» (ማቴ.2፥2)፣ «የእስራኤል ንጉሥ» (ዮሐ.1፥49)።

«ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚመጣ በሰሙ ጊዜ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው ሆሣዕና በጌታ ስም የሚመጣ የእስራኤል ንጉሥ በማለት ሊቀበሉት ወጡ» (ዮሐ.12፥13)።



www.ethiopianorthodox.org

__ትንቢታዊ ማስረጃ__፤ «አንች የጽዮን ልጅ ደስ ይበልሽ፤ አንች የኢየሩሳሌም ልጅ እልል በይ፤ እነሆ! ንጉሥሽ ይመጣልሻል፤ ጻድቅ መድኃኒትም እርሱ ነው፤ ድኃም ሆኖ በአህያም ተቀምጦ በአህያ ግልገል በውርንጭላይቱ» (ዘካ.9፥9)።

## የማይመስል «አምላክ»

«አምላክ» ተራበ!

«አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ተራበ» (ማቴ.4፥12)።

«በማለዳ ወደ ከተማ ሲመለስ ተራበ» (ማቴ.21፥18)።

«በማግስቱም ከቢታንያ ሲወጡ ተራበ» (ማር.1፥12)።

__ሐተታ__፤ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው፤ ፍጹም አምላክ እንደ መሆኑ እህል ውኃ ሳይቀምስ አርባ ቀንና ሌሊት ጾሟል፤ እንደ ሰውነቱ ደግሞ ተርቧል፤ ተጠምቷል፤ ክርስቶስ መጾሙ ክብር ሊያገኝበት አይደለም፤ ለተከታዮቹ ክርስቲያኖች የጾምን ሕግና ሥርዓት ለማስተማርና ሰይጣንም ድል የሚሆነው በጾምና በጸሎት መሆኑን ለማስገንዘብ፤ እኔ ሰይጣንን በጾም ድል እንዳደረግሁት እናንተም በጾም በጸሎት ድል አድርጉት ለማለት ምሳሌ ለመሆን ነው።

ደቀ መዛሙርቱ ሊያወጡት ያልቻሉትን ሰይጣን ክርስቶስ ገሥፆ ካስወጣው በኋላ፤ «ይህ ዓይነቱ ባላጋራ ‹ሰይጣን› በጾምና በጸሎት ካልሆነ በስተቀር አይወጣም» ብሏቸዋል (ማቴ.17÷14–21)።

## «አምላክ» ተጠማ!

«ተጠማሁ አለ» (ዮሐ.19፥28)።

__ሐተታ__፤ ውኃ ከድንጋይ አፍልቆ መና ከደመና አውርዶ እስራኤልን በምድረ በዳ የመገበ አምላክ ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተገልጦ ቢያስትምራቸው አንቀበልም በማለት ጠልተው ተመቀኝተው በመስቀል ሲሰቅሉት ተጠማሁ አለ፤ ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ሆምጣጤ አጠጡት፤ ትንቢቱ «በምግቤ ሐሞት ጨመሩ፤ ለጥማቴም ሆምጣጤ አጠጡኝ» ይላል (መዝ.69፥21)።



## «አምላክ» አንቀላፋ!

«እርሱ ግን ተኝቶ ነበር (ማቴ.8፥24)።

«እርሳቸው ሲሄዱ እርሱ አንቀላፋ፤...» (ሉቃ.8፥23)።

«እርሱም በስተኋላው ትራስ ተንተርሶ ተኝቶ ነበር» (ማር.4፥38)።

__ሐተታ__፤ አምላክ አያንቀላፋም፤ ደቀ መዛሙርቱን ለመፈተንና በባሕርና በነፋሳት ላይ ሥልጣን ያለው መሆኑን ለማሳየት ነው፤ ሰው እንደ መሆኑ መጠን አንቀላፋ፤ አምላክ እንደ መሆኑ ደግሞ ባሕርንና ነፋሳትን ገሥፆ፤ ፀጥ አደረጋቸው፤ «እነሆ በባሕሩ ታላቅ መናወጥ ሆነ፤ ከሞገድ የተነሣ ማዕበሉ መርከቡን እስቲደፍነው ድረስ፤ እርሱ ግን አንቀላፍቶ ነበር፤ ደቀ መዛሙርቱ ወደርሱ ቀርበው አቤቱ ልናልቅ ነውና አድነን ሲሉ ቀሰቀሱት፤ እርሱም ለምን ትፈራላችሁ? እናንተ ሃይማኖት የጎደላችሁ በማለት ተነሥቶ ባሕሩንና ነፋሳቱን ገሥፃቸው፤ ታላቅ ፀጥታ ሆነ፤ ሰዎችም ይህ ማነው? ባሕርና ነፋሳት የሚታዘዙለት ሲሉ አደነቁ» (ማቴ.8፥24–27)።

## «አምላክ» ታከተው!

«ኢየሱስም መንገድ ከመሄድ ደክሞ በጉድጓድ አጠገብ ተቀመጠ» (ዮሐ.4፥6)።

__ሐተታ__፤ ክርስቶስ ሰው እንደ መሆኑ መጠን መድከም መብላት መጠጣት ነበረበት፤ «ኢየሱስ በሰማርያ በኩል ሲያልፍ በያዕቆብ ምንጭ አጠገብ ሲደርስ አረፍ አለ፤ ደክሞት አይደለም፤ ውኃ ቀጂውን እንጨት ሰባሪውን ለማስተማር ነው፤ አረፍ እንዳለ አንዲት ሴት ውኃ ልትቀዳ ከሰማርያ መጣች፤ ኢየሱስም ውኃ አጠጭኝ አላት፤ ደቀ መዛሙርቱ እንጀራ ሊገዙ ወደ መንደር ሄደው ነበር፤ ሴቲቱም እንዴት አንተ አይሁዳዊ ስትሆን ከእኔ ውኃ ትጠጣለህ? እኔ የሰማርያ ሴት ነኝ፤ አይሁድ ከሰማርያ ሰዎች ጋር አይገናኙምና አለችው፤ ኢየሱስም የእግዚአብሔርንስ ጸጋ ብታውቂ ውኃ አጠጭኝ የሚልሽ ማን እንደሆን



www.ethiopianorthodox.org

አንች ትለምኚው ነበርሽ፣ እርሱም የሕይወት ውኃ ይሰጥሽ ነበር አላት፣ ሴቲቱም አቤቱ መቅጃ የለህም፣ ምንጩም ጥልቅ ነው፣ የሕይወት ውኃ ከወዴት ታገኛለህ? አንተ ካባታችን ከያዕቆብ ትበልጣለህን? ይህን ምንጭ የሰጠን እርሱ ነው፣ ከዚህ ምንጭ እርሱም፣ ልጆቹም እንስሶቹም ጠጡ አለችው፣ ኢየሱስም አላት ከዚህ የሚጠጣ ዳግመኛ ይጠማል፣ እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ግን ለዘላለም አይጠማም፣ እኔ የምሰጠው ውኃ ለዘላለም በውስጡ ይመነጫል እንጂ አላት፣ ሴቲቱም አለችው ይህን ውኃ ስጠኝ ዳግመኛ እንዳልጠማ ውኃ ለመቅዳትም ወደዚህ እንዳልመጣ፣ ኢየሱስም ሂጂና ባልሽን አምጭ አላት፣ ሴቲቱም ባል የለኝም አለችው፣ ኢየሱስም ባል የለኝም ማለትሽ መልካም ነው፣ አምስት ባሎች ነበሩሽና፣ ዛሬም ካንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም፣ ይህንስ እውነት ተናገርሽ አላት፣ ሴቲቱም አለችው አቤቱ እኔ አይሃለሁ አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ፣ እናንተም ትላላችሁ አባቶቻችን በዚህ ተራራ ስገዱ በኢየሩሳሌም ስፍራ እንዳለ ሊሰገድበት የሚገባው፣ ኢየሱስም አላት አንች ሴት እመኝኚ ጊዜ እንድትመጣ በዚህ ተራራ በኢየሩሳሌም ለአብ የሚሰግዱባት፣ እናንተ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፣ እኛ ግን ለምናውቀው እንሰግዳለን፣ መድኃኒት ከአይሁድ ነውና፣ ነገር ግን ጊዜ ትመጣለች፣ እርሷም አሁን ናት፣ ለአብ በመንፈስ በውነትም የሚሰግዱባት፣ አብ እንደነዚህ ያሉትን የሚሰግዱለትን ይሻልና፣ እግዚአብ.፡-ር መንፈስ ነው፣ የሚሰግድለትም በመንፈስ በውነትም ይገባል ይሰግዱለት ዘንድ፣ ሴቲቱም አለችው፣ አውቃለሁ መሲሕ ክርስቶስ እንዲመጣ ያም በመጣ ጊዜ ሁሉን ያስትምረናል፣ ኢየሱስም እኔ ነኝ የምናገርሽ አላት»(ዮሐ.4፥4–26)።

## «አምላክ» ታወከ!

«ኢየሱስ በመንፈስ አዘነ፣ ዕንባውንም አፈሰሰ» (ዮሐ.11፥33–35)።

<u>ሐተታ</u>፣ ክርስቶስ ወዳጁ አልዓዛር በሞተ ጊዜ እንደ ሰውነቱ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ፣ እንደ አምላክነቱ ደግሞ ከአራት ቀን በኋላ ከሞት አስነሣው (ዮሐ.11፥42–44)።



## «አምላክ» ተከዘ!

«ያዝንም ይተክዝም ጀመር» (ማቴ.26፥37)።

«ነፍሴ እስከሞት ድረስ አዘነች» (ማቴ.26፥38)።

<u>ሐተታ</u>፣ ነፍሴ (ሰውነቴ) እስከ ሞት ድረስ አዘነች ማለቱ የሥጋን ጠባይ መናገሩ ነው፡ ሥጋ ደካማ ነው፣ ነፍስ ግን ምን ጊዜም ዝግጁ ናት በማለት ደቀ መዛሙርቱ ወደፈተና እንዳይገቡ ነቅተው ተግተው እንዲጸልዩ መሳልሶ ነግሯቸዋል፣ አስጠንቅቋቸዋል (ዮሐ.26፥39–41)።

## ደካማ «አምላክ»!

«ከሰማይም የሚያጸናው መልአክ ታየው» (ሉቃ.22፥43)

<u>ሐተታ</u>፣ ለደካሞች ኃይልን የሚያሰጣቸው ኃያላኑን ደግሞ አቅም የሚነሳቸው የኃይል ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አባት ሆይ፣ ይህን ጽዋ ከእኔ አርቅልኝ ያንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ የእኔ ፈቃድ አይሁን እያለ ሲጸልይ መልአክ ከሰማይ ሆኖ ታየው ማለቱ ይህ ሁሉ የሥጋ ጠባይ ነው እንጂ የመለኮት ባሕርይ አይደለም፣ «እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ወደኔ ኑ፣ እኔ አሳርፋችኋለሁ፣ ቀንበሬን ተሸከሙ፣ ከኔ ተማሩ፣ እኔ የዋህ ነኝ ልቤም ትሑት ነውና፣ ለነፍሳችሁ ዕረፍት ታገኛላችሁ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና» (ማቴ.11፥28–30)።

## ጦረኛ «አምላክ»!

«የአይሁድ ፋሲካ ደርሶ ነበር፣ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ፣ በመቅደስም በሬዎችን በጎችንና ርግቦችን የሚሸጡትን ገንዘብ ለዋጮችንም ተቀምጠው አገኘ፣ የገመድ ጅራፍ አበጅቶ በሬዎችንና በጎችን ከመቅደስ አስወጣቸው፣ የለዋጮችንም ገንዘብ አፍስሶ፣ ጠረጴዛቸውን ገለባበጠ» (ዮሐ.2፥13–15)።

የአምላክ ክተት ዓዋጅ፣ «በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ ሰይፍን እንጂ» (ማቴ.10፥34)።

«የሌለውም ልብሱን ሸጦ ሰይፍ ይግዛ» (ሉቃ.22፥36)።



www.ethiopianorthodox.org

<u>ሐተታ</u>፤ ክርስቶስ ጦረኛ አምላክ አይባልም፤ የመጣለት ሥራው አይደለምና፤ ቀናተኛ አምላክ ቢባል ይስማማዋል፤ ምክንያቱም ንጉሥ በመንግሥቱ እግዚአብሔር በአምልኮቱ ቢገቡበት አይወድምና። አይሁድ የአባቱን ቤተ መቅደስ (የጸሎት ቤት) ገበያ በማድረጋቸው ተቆጥቶ ሻጮችንና ለዋጮችን ከቤተ መቅደስ አስወጣ፤ «የቤትህ ቅንዓት በላኝ» ተብሎ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ (መዝ.69፥9)።

ክርስቶስ የክተት ዓዋጅ አላወጀም፤ ጸሐፊው እንኳን ጥሬ ንባብ አግኝቶ ቀናውን አዛብቶ መናገር ይወዳል፤ «ሰይፍን እንጂ ሰላምን አላመጣሁም» ማለት በሃይማኖት ወንድ ልጅን ካባቱ፤ ሴት ልጅን ከናቷ፤ ምራትን ካማቷ እለያለሁ ማለቱ ነው፤ እንግዲህ እናት አባትና አማት ጥንቱን የሙሴን ሕግ አንለቅም ቢሉ ልጆች ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት ቢከተሉ በመካከላቸው መለያየት መጣ ማለት ነው፤ ልብሱን ሸጦ ሰይፍ ይግዛ ማለትም እንደዚሁ ነው፤ የሰይፍ አገልግሎት መቁረጥ መለያየት ነው፤ እናንተም ፈቃደ ሥጋችሁን ከፈቃደ ነፍሳችሁ ለዩ ቆራጦች ሁኑ ማለት ነው፤ ከዚህ በላይ ለቀረበው ሐተታ ዋናው ማረጋገጫ የክርስቶስ የሕይወት ታሪክ ሐዲስ ኪዳን ነው፤ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ 33 ዓመት ከ3 ወር ቆይቶ የመጣለትን ግዳጅ ፈጽሞ ወደ መጣበት ወደ ሰማያዊ ክብሩ እስቲመለስ ድረስ በዚህ ጊዜ በዚህ ስፍራ ብጥብጥ አስነሥቷል፤ ከእገሌ ጋር ጦር ተማዟል አልተባለም፤ አልተነገረለትም። በመጨረሻ ወንጌልን አስትምሮ ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት በመስቀል ላይ ራሱን ሠውቶ ሞትን በሞቱ ድል ነስቶና በሦስተኛው ቀን ተነሥቶ ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ።

## «አምላክ» በስጋት ተንከራተተ!!

«ከዚህ በኋላ ኢየሱስን አይሁድ ሊገድሉት ይፈልጉ ስለ ነበረ በይሁዳ መመላለሱን ትቶ በገሊላ ይመላለስ ነበር» (ዮሐ.7፥1)።

«እንግዲህ ከዚያ ቀን ጀምረው ሊገድሉት ተማከሩ፤ ኢየሱስም ከዚያ ወዲያ በአይሁድ መካከል ተገልጦ አልተመላለሰም» (ዮሐ.11፥53–54)።

<u>ሐተታ</u>፤ ክርስቶስ ጊዜው ሳይደርስ ያለ ጊዜው እንደማይሞት ስለሚያውቅ ጠላቶቹ አይሁድ ድንገት ቢያገኙትም በመካከላቸው ተሰውሮ ያልፍ ነበር (ዮሐ.3፥59)።



## «አምላክ» ከእጃቸው አፈተለከ!

«ደግመው ሊይዙት ፈለጉ፤ ከእጃቸውም ወጣ» 10፥39፤

«ስለዚህ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤ ኢየሱስ ግን ተሰወራቸው፤ ከመቅደስም ወጥቶ በመካከላቸው አልፎ ሄደ» (ዮሐ.8፥59)።

<u>ሐተታ ማስረጃ</u>፤ «አብርሃም አባታችሁ ቀኔን ያይ ዘንድ ተመኘ፤ አይቶም ደስ አለው አላቸው፤ አይሁድም ገና አምሳ ዓመት አልሞላህ አብርሃምን አየሁ ትላለህ? አሉት፤ ኢየሱስም እውነት እውነት እላችኋለሁ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው፤ በዚህ ጊዜ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤ ኢየሱስ ግን ተሰውሮባቸው ከመቅደስ ወጥቶ በመካከላቸው አልፎ ሄደ» (ዮሐ.8፥56–59)።

## የ«አምላክ» መማረክ

በተማሪው ክህደት አምላክ የተደበቀበት ቦታ ታወቀ፤ «ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ብዙ ጊዜ ወደዚያ ስለ ተሰበሰቡ አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳ ደግሞ ስፍራውን ያውቅ ነበር፤ ስለዚህ ይሁዳ ጭፍሮችን ከካህናት አለቆች ከፈሪሳውያንም ሎሌዎችን ተቀብሎ፤ በችቦና በጋሻ ጦርም ወደዚያ መጣ» (ዮሐ.18፥2–3)።

«አምላክ» ተማረከ፤ ታስሮም ተወሰደ፤ «እንግዲህ የሻለቃውና ጭፍሮቹ የአይሁድ ሎሌዎች ኢየሱስን ይዘው አሰሩት» (ዮሐ.18፥12–13)።

<u>ሐተታ</u>፤ ይሁዳ በፍቅረ ንዋይ ተታሎ መምህሩን አሳልፎ ቢሰጠውም ክርስቶስ ግን ሰው የሆነው ሊሞት ሊሰቀል ስለሆነ አያስገርምም፤ አይሁድም ያለ እርሱ ፈቃድ አንዳች ጉዳት ሊያደርሱበት የሚያስችላቸው አቅምና ብልሃት አልነበራቸውም።

«ኢየሱስም የሚመጣበትን ሁሉ አውቆ ወጣና ማንን ትፈልጋላችሁ? አላቸው፤ የናዝሬቱ ኢየሱስን እንፈልጋለን አሉት፤ ጠቁሞ ያስያዘው ይሁዳም ከነርሱ ጋር ቆሞ ነበረ፤ ኢየሱስ እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ ሁሉም ወደ ኋላቸው ተመልሰው በጀርባቸው ወደቁ፤ ከወደቁበት ተነሥተው እንደ ገና በፊቱ ቆሙ፤ እርሱም እንደ ገና ማንን ትፈልጋላችሁ? ሲል ጠየቃቸው፤ እነሱም የናዝሬቱ ኢየሱስን ነው



www.ethiopianorthodox.org

አሉት፣ ኢየሱስም እኔ ነኝ አላልኋችሁምን? እኔን የምትሹ ከሆናችሁ እነዚህን ተዋቸው ይሂዱ አላቸው...»ከዚህ በኋላ የሻለቃው ጭፍሮችና የአይሁድ ሎሌሎች ተረባርበው ይዘው አሰሩት «አንድ ለእናቱ ‹የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ› አቅማቸውን አሳውቆ በፈቃዱ እጁን ሰጣቸው (ዮሐ.18፥4–12)።

## «አምላክ» ተዋረደ

«ኢየሱስንም የያዙት ሰዎች ይዘብቱበትና ይደበድቡት ነበር፤ ፊቱንም ሸፍነው ማነው የመታህ በማለት በጥፊ ይመቱት ነበር» (ሉቃ.22፥63–64)።

«በዚያን ጊዜ በፊቱ ተፉበት፤ ጎሰሙትም፤ ሌሎችም በጥፊ መቱት» (ማቴ.26፥67)።

<u>ሐተታ</u>፤ እግዚአብሔር አዳምን በአምሳሉ ፈጥሮ የምድር ገዥ እንደራሴ አድርጎት ነበር፤ ይሁን እንጂ አዳም የተሰጠውን ትእዛዝ ተላልፎ ሌላ ሥልጣን ሲሻ በመገኘቱ በነፍሱም በሥጋውም እስራትና ግዞት ተፈረደበት፤ የፈጠረው አምላክ የደረሰበትን ውርደት አይቶ ልቅሶውን ሰምቶ የአዳምን ሥጋ በመበልስ አዳም ሊቀበለው የሚገባውን ውርደተና መከራ በአደባባይ ተቀበለ፤ ጠላቶቹ ለጊዜው ምክንያት ያደረጉት «አምላክ ነኝ የአምላክ ልጅ ነኝ» ብለሃል የሚል ነው፤ ክርስቶስ ግን አምላክ ወልደ አምላክ መሆኑን በተግባር እያሳየ አስተምሯቸዋል፤ «እኔና አብ አንድ ነን»ቢላቸው አይሁድ ግን ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤ ኢየሱስም መልሶ ብዙ መልካም ሥራ ከአባቴ ዘንድ አሳየኋችሁ፤ ከርሳቸው ስለማናቸው ሥራ ነው የምትወግሩኝ? አላቸው፤ ስለ መልካመ ሥራህ የምንወግርህ አይደለም፤ አንተ ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ አድርገህ በመሳደብህ ነው እንጂ አሉት፤ ኢየሱስም አላቸው አብ የቀደሰውን ወደ ዓለምም የላከውን እንዴት ትሳደባለህ ትላላችሁ? የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልሁ፤ የአባቴን ሥራ ባልሠራ አትመኑብኝ፤ እኔን ባታምኑም በሥራዩ እመኑ፤ እንድታውቁ እና እንድታምኑም አብ በኔ እንዳለ እኔም በአብ» (ዮሐ.10፥30–38)።



## «አምላክ» አማረረ!!፣ መድረሻ አጣ!!

«ይህን ሲል በዚያ ቆሞ የነበረው ከሎሌዎቹ አንድ ለሊቀ ካህናቱ እንዲህ ትመልሳለህ በማለት ኢየሱስን በጥፊ መታው፤ ኢየሱስም መልሶ ክፉ ተናግሬ እንደሆን ስለ ክፉ መስክር፤ መልካም ተናግሬ እንደሆን ግን ስለ ምን ትመታኛለህ?» (ዮሐ.18፥22)።

<u>ሐተታ</u>፤ ክርስቶስ በዚህች ምድር በቆየባት 33 ዓመት ከ3 ወር የሕይወት ታሪኩ ‹ሐዲስ ኪዳን› እንደሚያስረዳን ከመልካም ሥራውና አምላክነቱን ከመግለጡ በቀር አንዲት ጥፋት እንዳላገኙበት ጠላቶቹም አረጋግጠዋል?

## «አምላክ» ሞት ተፈረደበት!!

«እነርሱ ሁሉ ሞት ይገባዋል ብለው ፈረዱበት» (ማር.14፥64)።

«እነርሱ ሞት ይገባዋል ብለው መለሱ» (ማቴ.26፥66)።

<u>ሐተታ</u>፤ ብዙ የሐሰት ምስክሮች ተፈልገው አልተገኙም፤ ሁለት ምስክሮች ቀርበው ይህ የእግዚአብሔርን ቤት አፈርሰው ዘንድ በሦስት ቀንም እሠራው ዘንድ እችላለሁ ብሎአል አሉ፤ የካህናት አለቃም መልሶ በሕያው እግዚአብሔር እለምንሃለሁ አንተ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ንገረኝ አለው፤ ኢየሱስም አንተ አልህ (መሰከርህ) እኔ እላችኋለሁ፤ ከዚህ በኋላ የሰው ልጅ በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይ ደመናም ሲመጣ ታያላችሁ አለው፤ በዚህ ጊዜ የካህናቱ አለቃ ልብሱን ቀዶ እነሆ! ስድቡን ሰምታችኋል፤ ምን ምስክር ያስፈልጋል? እንግዲህ ምን ትላላችሁ? አለ፤ ሁሉም ሞት ይገባዋል አሉ» (ማቴ.26፥60–66)።

## የ«አምላክ» የጣር ጩኸት

«ኢየሱስ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ይህም አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ? ማለት ነው» (ማቴ.27፥46)።

<u>ሐተታ</u>፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው፤ ፍጹም ሰው እንደ መሆኑ መጠን «አምላኬ አምላኬ

www.ethiopianorthodox.org

ለምን ተውኸኝ» ብሏል፣ የሰውነት ጠባይ ነው፤ ፍጹም አምላክ እንደ መሆኑ መጠን ደግሞ «ከ6 ሰዓት እስከ 9 ሰዓት ፀሐይ ጨለመች፤ ብርሃኗን ከለከለች)፣ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ለሁለት ተቀደደ፤ ምድር ተናወጠች፣ ሕንፃዎች ተሰነጠቁ፣ መቃብሮች ተከፈቱ፣ ሙታን ተነሡ፣ አምላክነቱን መሰከሩ፣ የመቶ አለቃውና ከርሱ ጋር የነበሩት ሁሉ የሆነውን ሁሉ አይተው እጅግ ፈሩ፣ ይህ በእውነቱ የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ አሉ» (ማቴ.27፥45–54)።

## «አምላክ» እንደ ገራም እንስሳ!

«እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፤ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል አፉን አልከፈተም» (የሐ.8፥32)።

<u>ሐተታ</u>፣ የክርስቶስ ሞት እንግዳ ደራሽ ውኃ ፈሳሽ አይደለም፣ ቀደም ሲል ሰማያዊ አምላክ ምድራዊ ሥጋን ለብሶ ስለ ሰው ልጆች መከራ እንደሚቀበል ነቢያት ትንቢት ተናግረዋል፤ ከነዚህ አንዱ ኢሳይያስ «በውነት እርሱ ደዌያችንን ወሰደ፤ ሕማማችንን ተሸከመ፤ እኛም እንደ ተመታ ቈጠርነው፤ እግዚአብሔር እንደ ቀሠፈው እንደ ተዋረደውም፤ እርሱ ግን ስለ ኃጢአታችን ተወጋ፤ ስለ ዓመፃችንም ተደቀቀ፤ የደኅንነታችን ተግሣፅ በርሱ ላይ ነው፤ በርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን፤ እኛ ሁላችን እንደ በግ ጠፋን፤ ሁሉ ወደ መንገዱ አዘነበለ፤ የሁላችንንም ኃጢአት እግዚአብሔር በርሱ ላይ አኖረበት፤ ተጨነቀ፤ ተሠቃየም፤ አፉንም አልከፈተም፤ እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፤ እንደ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንዲል አፉንም አልከፈተም» ሲል አስቀድሞ ትንቢት ተናግሯል(ኢሳ.53፥4–7)።

«በማግስቱም ዮሐንስ ኢየሱስ ወደርሱ ሲመጣ አይሆ እነሆ የእግዚአብሔር በግ የዓለሙን ኃጢአት የሚያስወግድ አለ» (ዮሐ.1፥29)።

## «አምላክ» ሞተ ተብሎ ተገመተ!

ሟች አምላክ፤ «ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ነፍሱንም ሰጠ» (ማር.15፥37)።

«ክርስቶስ ስለ እኛ ስለ ኃጢአተኞች ሞቷልና» (ሮሜ.5፥6)።



«ወደ ኢየሱስ ግን በመጡ ጊዜ እርሱ ፈጽሞ እንደ ሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩትም» (ዮሐ.19፥33)።

<u>ሐተታ</u>፣ «ስለዚህ አብ ይወደኛል፣ ነፍሴን እሰጣለሁና ደግሞ እወስዳት ዘንድ ሥልጣን አለኝ፣ ማንም ከእኔ አይወስዳትም፣ ነገር ግን በፈቃዴ አሰጣታለሁ፤ አነሳት ዘንድ ሥልጣን አለኝ፣ ደግሞ እወስዳት ዘንድ» (ዮሐ.10፥17–18)።

የሙስሊሙ አፈቀላጤዎች ባንድ በኩል ክርስቶስ አልሞተም አልተሰቀለም እያሉ ይከራከራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ሞቱንና ስቅለቱን የሚያረጋግጡ አንቀጾችን እየጠቀሱ ማወናበድ ምን ይባላል? አልወድሽም አልሰድሽም ነው፣ «ማን ይንገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ» ነውና በመስቀል ላይ ሰቅለው የገደሉት አይሁድ እንኳ ሞቱንና ስቅለቱን አልደበቁም፤ ሊደብቁ የሞከሩት ነገር ቢኖር ትንሣኤውን ብቻ ነበር፤ ነገር ግን ትንሣኤውንም ደብቀው ሊያስቀሩት አልቻሉም፤ ወዲያው ይፋ ወጥቷል።

የሞተላቸውና ደሙን ያፈሰሰላቸው ክርስቲያኖችም ሞቱንና ትንሣኤውን በደስታና በጸጋ ተቀብለው ድነውበታል፤ ተጠቅመውበታል። የሦስተኛው አካል ረድፍ ማለት የሙስሊሙ ኅብረተሰብ አፈቀላጤዎች ግን ከ600 ዓመታት በኋላ ተነሥተው በማያገባቸው ገብተው ክርስቶስ አልሞተም አልተሰቀለም በማለት የክርክር መድረክ መክፈታቸው ምን ይባላል? ከምን ዓይነት የአገልግሎት ዘርፍ ይፈርጅልናል ብለው ነው? ክብር መስጠታቸው ነው? ወይስ ለክርስቶስ ሕይወት ቀንተው? ታላቅ ድንቁርና ነው!

አንደኛ፣ በመሠረቱ አምላክነቱን ያለመቀበላቸው ፍጹም ክህደት ነው፣

ሁለተኛ፣ አያገባቸው ገብተው ሞቱን ስቅለቱን ለማስተባበል መሞከራቸው በኃጢአት ላይ ኃጢአት ነው።

## የ«አምላክ» አስከሬን

«ይህ ሰው ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው፤ ጲላጦስም ሥጋውን ይሰጡት ዘንድ አዘዘ፤ ዮሴፍም ሥጋውን ወስዶ በንጹ በፍታ ከፈነው፤ ባዲስ መቃብርም አኖረው» (ማቴ.27፥58–60)።

www.ethiopianorthodox.org

**ሐተታ**፣ ዓርብ በ11 ሰዓት ላይ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የተባሉ ሁለት ደጋግ (ቅዱሳን) ሰዎች ከመስቀል ላይ አውርደው በነጭ ልብስ ከፍነው ቀብረውታል፤ ክርስቶስ ሰው እንደ መሆኑ መጠን ሞቷል፣ ተቀብሯል፤ አምላክ እንደ መሆኑ መጠን ደግሞ ሞትና መቃብር ይዘው ሊያስቀሩት አልቻሉም፤ በገዛ ሥልጣኑ ተነሥቷል፤ ወደ ሰማይ ዐርጓል፤ ባባቱ ቀኝ ተቀምጧል፤ መልካም ለሠራ ዋጋውን፣ ክፉ ለሠራ ፍዳውን ለመክፈል ዳግመኛ ይመጣል (ማቴ.26፥31–46)።

## ሊታዘንለት የሚገባ «አምላክ»!

«የመቶ አለቃውም የሆነውን ሁሉ ባየ ጊዜ ይህ ሰው በውነት ጻድቅ ነበረ ብሎ እግዚአብሔርን አከበረ» (ሉቃ.23፥47)።

**ሐተታ**፣ ክርስቶስ እዘኑልኝ አልቅሱልኝ አላለም፣ አይሁድ ክርስቶስን በቀራንዮ ሊሰቅሉት መስቀሉን አሸክመው ይዘውት ሲሄዱ፤ «እጅግ ብዙ ሕዝብ ይከተለው ነበር፣ ሴቶችም ያለቅሱለት ዋይም ይሉ ነበር፤ ኢየሱስም ወደርሳቸው ተመልሶ እላንት የኢየሩሳሌም ልጆች ‹ሴቶች› ለእኔ አታልቅሱልኝ፣ ነገር ግን ስለ ራሳችሁ አልቅሱ፣ ስለ ልጆቻችሁም፤ እነኋት ቀን ትመጣለች፣ የሚሉባት ለመካኖች ላልወለደች ማኅፀን ላላጠቡ ጡቶችም ምስጋና ይገባቸዋል የሚሉባት ቀን ትመጣለች፣ ያን ጊዜ ተራሮችን በላያችን ውደቁ ኮረብቶችንም ድፈኑን ይሏቸዋል» (ሉቃ.23፥26–30፤ ሆሴ.10፥8)።

## ማጠቃለያ

የደቡብ አፍሪቃው ሰባኪ «ኢየሱስ አምላክ ነው» አለ፤ እንዴት? ቢሉት

1ኛ. የአምላክን ባሕርያት በመጋራቱ፤

2ኛ. በሁሉም መልኩ አምላክን (እግዚአብሔርን) ስለሚመስል ነው ይላል፤

ነገር ግን እስካሁን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ኢየሱስ ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች ኢየሱስ የአምላክን (የእግዚአብሔርን) ባሕርያት የማይጋራና በምንም ዓይነት አምላክን እንደማይመስል በማያሻማ መልኩ የሚያረጋግጡ ሆነው እናገኛቸዋለን። ፈጣሪም እንዳልሆነ በቁርጠኝነት



www.ethiopianorthodox.org



መስክረዋል፤...ጠፍ፣ የሚቆላ ምላሱን እያንጣጣ ከላይ ወደ ታች ከታች ወደ ላይ ቢዘል»ኢሳ አላህ ነው» ብሎ ሙስሊሞችን ማሳመን ከቶውንም ቢሆን የሚቻል አይደለም ኢሳ ወደ እስራኤል ሰዎች አንድ መሠረታዊ ብሥራት አንግቦ የመጣ መሆኑን ሙስሊሞች በጽኑ ያምናሉ፤ ያም በምድር ላይ የአላህ መንግሥት እንደሚመጣ የሚያመለክት ትንቢት ሲሆን በነቢዩ ሙሐመድ መነሣት እውን ሆኗል፤ ይህ ነው የማያወላውለው የሙስሊሞች እምነት ተብሏል።

**ሐተታ**፣ አህመድ ዲዳት የፈጠረው የደቡብ አፍሪቃው ሰባኪ የመላውን ዓለም ክርስቲያኖች አይወክልም። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ተጋሪ (ሸርክ) አይባልም፣ ወልድ (ክርስቶስ) ከአብ ከባሕርይ አባቱ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ከባሕርይ ሕይወቱ ጋር እኩል ባሕርይ እኩል ሥልጣን እኩል አገዛዝ ያለው የባሕርይ አምላክ ነው።

ሙስሊሞች አንሰማም አንለማም የገዛሆን ጆሮ ይስጠን አላችሁ እንጂ ከሰማችሁማ እነሆ «እኔና አብ አንድ ነን»፤ «ፊልጶስም አለው አብን አሳየንና ይበቃናል፣ ኢየሱስም አለው እኔን ያየ አብን አየ፣ አታምንምን? እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ፣ የምነግራችሁን ነገር ከእኔ አልናገርም አብ በእኔ ያደረብኝ እራሱ ሥራውን ይሠራል እንጂ፤ በእኔ እመኑ፣ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ ወይም ስለ ሥራዬ በእኔ እመኑ። እኔ መንገድ ነኝ እውነትም ሕይወትም፣ በእኔ በኩል ካልሆነ በስተቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። ያባቴን ሥራ ባልሠራ አትመኑብኝ፣ በእኔ ባታምኑ በሥራዬ እመኑ፣ እንድታውቁ እንድታምኑም አብ በእኔ እንዳለ እኔም በአብ»፣ «አብ በማንም አይፈርድም፣ ነገር ግን ፍርዱን ሁሉ ለልጁ ሰጠው»፣ «እግዚአብሔር እንዲሁ ዓለሙን ወዷልና አንድ ልጁን እስቲለውጥ ድረስ በርሱ ያመነ ሁሉ እንዳይጠፋ የዘላለም ሕይወት ትሆንለት ዘንድ እንጂ።»

«አስቀድሞ ቃል ነበር፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፣ ይህ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፣ ሁሉ በርሱ ሆነ፣ ያለ እርሱ ምንም የሆነ (የተፈጠረ) የለም፣ ሕይወት በርሱ ነበረች፣ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች፣...ቃልም ሥጋ ሆነ፣ በእኛም

ላይ አደረ፣ ክብሩንም አየነ አንድ እንደ መሆኑ ከአብ ጸጋና ክብር የተሞላበት»… «ከሰማይም ድምፅ መጣ፣ እንዲህ ሲል፣ ይህ ነው የምወደው ልጄ ደስታዬን የማይበት።»

ሐዲስ ኪዳንን በሙሉ መጥቀስ ይቻላል፣ ይሁን እንጂ ዓይኑን አፍጥጦ ጆሮውን ዘግቶ ለሚያሾፍ ሙስሊም ጸሐፊ ከዚህ የበለጠ መጮህ አያስፈልግም፣ አውቆ የተደበቀ ቢጠሩት ወይ አይልም ይባላል (ዮሐ.10፥30፤ 14፥8–11፤ 14፥6፤ 10፥37፤ 5፥22፤ 3፥16፤ 1፥1–14፤ ማቴ.3፥17፤ ተመልከት)።

ክርስቶስ ወደ እስራኤል ይዞት የመጣው ብሥራት (የምሥራች) ከዓረቦች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም። ተስፋ የተሰጠውም ሆነ ትንቢት የተነገረው ለእስራኤል ብቻ ነው። እግዚአብሔር ኪዳኑንም ያጸናው ከእስራኤል ጋር ነው፣ ጥንት ተስፋ የሰጠው ትንቢት ያናገረውና ኪዳኑንም ከእስራኤል ጋር ያጸናው የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ጊዜው ሲደርስ በዳዊት በሰሎሞን ከተማ በኢየሩሳሌም ተወልዶ በአስራኤል መካከል ወንጌልን አስተምሮ በመጨረሻ ለሰው ልጆቹ ቤዛ በአይሁድ እጅ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞቷል፣ በሦስተኛው ቀን ተነሥቷል፣ ወደ ሰማይ ዐርጓል፣ ትንቢቱም ሆነ ምሳሌው በዚሁ በክርስቶስ ሞት በክርስቶስ አዳኝነት ተፈጽሟል፤ (አክትሟል)፤ እስልምና 600 ዓመታት ወደ ኋላ ተመልሶ ሊቀናቀነውና ሊከራከረው አይችልም፣ ይህ የሙሐመድ ዓላማ አልነበረም፣ የሙስሊሙ አፈቀላጤዎች ሕልም ነው፣ ሕልም ደግሞ አይከለከልም።



## ክፍል ሁለት

# «ክርስቶስ» ስም አይደለም፣ ‹የዮናስ ምልክት›

«ባሁን ወቅት በዓለም ላይ የሚገኙ ከአንድ ሺህ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት የክርስትና እምነት ተከታዮች የናዝሬቱ ኢየሱስ ‹ክርስቶስ› እንደ ሆነ በጭፍን ይቀበላሉ፤ ለዚህም አቋማቸው ማጠናከሪያ ይሆኑ ዘንድ ‹አንድ ሺህ አንድ› ትንቢቶችን ከአይሁድ መጽሐፍ ቅዱስ ‹ከብሉይ ኪዳን መጽሐፍ› እየለቃቀሙና እየገጣጠሙ ኢየሱስ አዳኛቸው ‹መሲሐቸው› መሆኑን በመረጃ ለማስደገፍ ይፍጨረጨ ራሉ፤ ‹አንድ ሺህዎችን› ትንቢቶች ለጊዜው ወደ ጎን አድርገን ኢየሱስ ራሱ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ በማያሻማ ሁኔታ እርሱን ማንነት ሊያረጋግጥ የሚችል ምልክት እንደሚያሳይ ለአይሁድ ቃል ገብቶላቸው ነበር፤ የገባላቸውን ቃል ኪዳን ፈጽሞላቸው እንደሆነ ላንድ አፍታ እንመርምር፤

መጀመሪያ «ክርስቶስ» የሚለው ቃል ተውላጠ ስም ያለ መሆኑን መረዳት አለብን፤ ገላጭ ቅጽል ነው፤ (ክርስቶስ) የሚለው የግሪክ ቃል (መሲሕ) የሚለው የእብራይስጥ ቃል ቀጥተኛ ትርጉም ነው፤ በእንግሊዘኛ "Anointed" የሚለው ቃል የሚተካው ሲሆን ወደ አማርኛ ሲመለስ ደግሞ ‹የተቀባ› የሚል ትርጓሜ ይኖረዋል፤ ያተቀባ ማለት በግሪክ ቋንቋ ክርስቶስ ማለት እንደሆነ ተጠቅሷል፤ እንግሊዘኛ ተናጋሪዎች "Christos" ‹ክርስቶስ› ከሚለው የግሪክ ቃል ውስጥ (O) እና (S)ን በማውጣት "Christ" «የሚል አዲስ ቃና ያለው ቃል እንደ ፈጠሩ መገንዘብ አያዳግትም» ተብሏል።

<u>ሐተታ</u>፤ ክርስቲያኑ ኅብረተሰብ በጭፍን አይመራም፤ ራሱን አያታልልም፤ በጭፍን የምትመሩ እናንተው የሙስሊሙ አፈቀላጤዎች ናችሁ፤ እናንተ እንደምትሉት በብሉይ ኪዳን አንድ ሺህ አንድ

www.ethiopianorthodox.org

ትንቢቶች የተነገሩለት ለክርስቶስ ነው፣ ለሙሐመድ ግን አንዲት ቃል አልተነገረለትም፣ በብሉይ ኪዳን ለክርስቶስ የተነገረውን ትንቢት እየለቃቀማችሁ የእኛ ነው በማለት ቀን በቀን ዘረፋውን ተያይዛችሁታል፣ ነገር ግን ሀብተ ትንቢት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ በረከት እንጂ ወርቅ ብር ባለ መሆኑ ከላይ ከእግዚአብሔር ካልተሰጠ በስተቀር ማንም በጉልበቱ ነጥቆ የራሱ ገንዘብ ሊያደርግ አይችልም።

አንድ ሺህ አንድ ትንቢቶች ሙሐመድን ስለማይመለከቱትና ስለማይጠቅሙት እናንተው ወደ ጎን ተዋቸው እንጂ በእኛ በክርስቲያኖች ዘንድማ በክርስቶስ ተፈጽመዋል፣ በተግባር ላይ ውለዋል፣ ክርስቶስ ማለት የተቀባ ማለት ነው ተብሏል፣ ወሳኙ የክርስቶስን አምላክነት መቀበል ያለ መቀበሉ ላይ ነው፣ የክርስቶስን አምላክነት የማይቀበል መናፍቅ ‹ሙስሊም› ተቀባ ከበረ ከሚለው ትችት ውስጥ ምን አገባው? ክርስቶስ የሚለው ቃል ከግሪክ ቋንቋ የተወረሰ ወይም በፊደል ፎርሙላ የወጣለት ስም አይደለም፣ ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት በትንቢት የወጣለት ስም ነው፣ «እወቅ አስተውልም፣ ከነገሩ መውጣት ጀምሮ ኢየሩሳሌም ተመልሳ እንድትሠራ እስከ ንጉሡ እስከመሢሕ ‹ክርስቶስ› ድረት ሰባት ሱባኤ ነው፣ ከ62 ሱባኤ በኋላ ጐዳናውና ቅፅሩ ይሠራል፣ ከ62 ሱባኤ በኋላ መሢሕ ተወግቶ ይሞታል» (ዳን.9፥25–26)።

«ሴቲቱም አለችው አውቃለሁ መሢሕ ክርስቶስ የሚሉት እንዲመጣ፣ እርሱም በመጣ ጊዜ ሁሉን ያስትምረናል፣ ኢየሱስም አላት እኔ ነኝ የምናገርሽ» (ዮሐ.4፥25–26)።

ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ «መልአኩም አላቸው አትፍሩ፣ እነሆ እኔ የሕዝብ ሁሉ የሚሆን ታላቅ የደስታ ምሥራች እነግራችኋለሁና፣ ዛሬ መድኃን ተወልዶላችኋል እርሱም ክርስቶስ ጌታ በዳዊት አገር» (ሉቃ.2፥10–11)። እውነቱን ለማወቅ ከተፈለገ ይህ ከዚህ በላይ የቀረበው ማስረጃ በቂ ነው።

## የዮናስ ምልክት (ተአምር እንደ ማስረጃ)

ከአይሁድ ወገን የሆኑ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ኢየሱስ ተአምር እንዲያሳያቸው ጠየቁት፣ «መምህር ሆይ! ከአንተ ምልክት እንድናይ



እንፈልጋለን አሉት» (ማቴ.12፥38)። እነሱ የፈለጉት አስማተኞች የሚያሳዩትን ዓይነት ምትሐታዊ ትርኢት ነበር፣ ኢየሱስ ግን «ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፣ ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም፣ ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ እንዲሁም የሰው ልጅ በከርሠ መቃብር ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል» (ማቴ.12፥39–40)። ኢየሱስ ለአይሁድ በሰጠው ግልጥ መልስ መሢህነቱን ለማረጋገጥ የርሱን ፍጻሜ ከዮናስ ፍጻሜ ጋር አመሳስሎ ነው ያቀረበላቸው።

<u>ሐተታ</u>፣ ከዕለታት አንድ ቀን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ መቅደስ ሲያስተምር የካህናት አለቆችና የሕዝቡ ሽማግሌዎች ወደ ርሱ ቀርበው በምን ሥልጣን ይህን ታደርጋለህ? ይህንስ ሥልጣን ማን ሰጠህ? አሉት፣ ኢየሱስም እኔም አንዲት ነገር እጠይቃችኋለሁ አለና «የዮሐንስ ጥምቀት ከወዴት ነበረች? ከሰማይ? ወይስ ከሰው? አላቸው። እነርሱ ግን በልባቸው አሰቡ፣ ከሰማይ ነው ብንለው እንግዲያው ለምን አላመናችሁትም? ይለናል፣ ከሰው ነው ብንለውም ሕዝቡን እንፈራለን፤ ሁሉም ዮሐንስን እንደ ነቢይ ያዩታልና፣ ከወዴት እንደ ሆነች አናውቅም አሉት፣ እኔም ይህን በምን ሥልጣን እንደማደርግ አልነግራችሁም አላቸው» (ማቴ.21፥23)።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምልክት ‹ተአምር› እንዲያሳያቸው አይሁድ ጥያቄ አቅርበውለት የሰጣቸው መልስና ይህ ከዚህ በላይ ጥያቄያቸውን በጥያቄ የመለሰላቸው ፍሬ ነገር ተመሳሳይ ነው። ምልክት ቢጠይቁት፣ «ዮናስ በዓሣ ሆድ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት እንደ ኖረ የሰው ልጅም ‹ክርስቶስ› በመቃብር ውስጥ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት ይኖራል» ሲል በነርሱ እጅ በመስቀል ተሰቅሎ እንደሚሞትና በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ ራሱን በዮናስ መቃብሩን በዓሣ ሆድ መስሎ አስረድቷቸዋል (ማቴ.12፥40)።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ዮናስን ይመስለዋል ማለት አይደለም፤ ምሳሌ ዘየሐፅፅ ‹ከፊል ምሳሌ› ነው፣ ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ የገባው ከነሕይወቱ ነው፣ ክርስቶስ ግን የተቀበረው ሞቶ ነው፤ ዮናስ ያን ጊዜ ባይሞትም ጊዜውን ጠብቆ ሞቷል፣ አልተነሣም። አምላክ



www.ethiopianorthodox.org

ዮናስ ክርስቶስ ግን ከሦስት ቀን በኋላ ሞትን ድል አድርጎ በራሱ ሥልጣን ተነሥቷል፤ ወደ ሰማይም ዐርጓል።

ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት አልሞላም ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ መነሻና መድረሻውን ባለማወቅ ነው እንጂ ሙሉ ነው፤ ክርስቶስ የተሰቀለ ዓርብ ቀን በ6 ሰዓት ነው፤ በተሰቀለ ጊዜ ከ6–9 ሰዓት ፀሐይ ጨልማለች፤ ክርስቶስ ዓርብ ከ9 ሰዓት በኋላ ፀሐይ እንደገና ብርሃኗን ሰጥታለች፤ ክርስቶስ ዓርብ በ11 ሰዓት ተቀበረ፤ እሑድ ከሌሊቱ በ10 ሰዓት እስከ 12 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ተነሥቷል (የማቴዎስ ትርጓሜ ወንጌል ምዕ.12፥41 ተመልከት)።

ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት መሆኑን በሰንጠረዥ አሳያለሁ፤

| መዓልት | ሌሊት |
|---|---|
| ዓርብ ከ3–6 ሰዓት፤ አንደኛ ቀን<br>ከ9–12 ሰዓት ብርሃን ሆኗል፤ ሁለተኛ ቀን<br>ቅዳሚ ሙሉ ቀን፤ ሦስተኛ ቀን | ዓርብ ከቀኑ 6–12 ሰዓት፤ አንደኛ ሌሊት<br>ቅዳሜ ሙሉ ሌሊት፤ ሁለተኛ ሌሊት<br>እሑድ ሙሉ ሌሊት፤ ሦስተኛ ሌሊት |

ለክርስትናው ዓለም ደቀ መዝሙር የምንሰጠው ትምህርት ይህ ነው፤ መናፍቃን ግን የማይገቡበት ቀዳዳ የማይፈነቅሉት ናዳ የለምና አያተጋንም።

እንዲያውስ «ክርስቶስ አምላክ አይደለም አልሞተም አልተሰቀለም» የሚል መናፍቅ፤ «ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት ሞልቷል አልሞላም» የሚል ጥያቄ አንሥቶ መከራከር መች ይገባው ነበር? መልስ መስጠትም ባልተገባ ነበር፤ ይሁን እንጂ መናፍቃንን መግቢያ ቀዳዳ መሮጫ ሜዳ ማሳጣትና አፋቸውን በመልስ መዝጋት አስፈላጊ በመሆኑ ተገቢው መልስ ተሰጥቶበታል።

## ዓውደ ዓመት

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው ዓርብ ቀን ነው፤ በዚህ ዓውደ ዓመት የክርስትናው ዓለም ይስማማል፤ ዓውደ ዓመት የሚባል ዓርብ ብቻ አይደለም፤ እሑድም ዓውደ ዓመት ነው፤ ዓርብ መከራ የተቀበለበት ሲሆን እሑድ ደግሞ ሞትን ድል አድርጎ በታላቅ ኃይል የተነሣበት በመሆኑ ታላቅ ዓውደ ዓመት ነው።



ፈረንጆች ዓርብን "Good Friday" መልካሙ ዓርብ ብለው ያከብሩታል፤ መልካም ዓርብ የተባለበት ምክንያት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ቤዛ ለመሆን ዓርብ ቀን በመስቀል ላይ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ለአባቱ ያቀረበበት ዕለት ስለሆነ ነው።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘጠኝ ሰዓት በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ነፍሱንም ከሥጋው በራሱ ሥልጣን ለየ (ሰጠ)። በ11 ሰዓት ላይ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የተባሉ ደጋግ ሰዎች ከጲላጦስ በማስፈቀድ በድኑን ከመስቀል አውርደው በነጭ ልብስ ከፍነው ጎልጎታ በተባለው ስፍራ ቀበሩት። ዮሴፍና ኒቆዲሞስ አይሁድን እሚፈሩ ስውር ደቀ መዛሙርቱ ነበሩ።

ለምን ሐዋርያት በቀብሩ ሥነ ሥርዓት አልተሳተፉም? ሐዋርያትማ አይሁድን ስለ ፈሩ ባካባቢው አልነበሩም፤ በዚህ ቀን የጌታቸውንና የመምህራቸውን የክርስቶስን አስከሬን አገላብጠው ከፍነው ሽቱ አርከፍክፈው እያለቀሱ እንዲቀብሩ የታደሉት (ሰማያዊ ጸጋና ክብር ያገኙ) ስውር ደቀ መዛሙርቱ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ብቻ ናቸው (ዮሐ.19፥38–42)።

ሸህ አህመድ ዳዲት የማያንኳኳው በር የማይሰበስበው ነገር የለም፤ በመልካሙ ዓርብ ፋንታ «መልካሙ ረቡዕ» በሚል ንውስ ርእስ ሚስተር ሮበርት ፋሂ የተባለውን የደርባን አገር ተወላጅ ነገረ ፈጅ አድርጎ በዓርብ ላይ የክርክር መድረክ ከፍቷል። ሚስተር ፋሂ ኢየሱስ ረቡዕ እንጂ ዓርብ እንዳልተሰቀለ ለማስረዳት መላምቱን ሲተነትን፤ አንድ ሰው ከእሑድ ጧት ጀምሮ ወደ ኋላ ቢቈጥር ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት የሚሆነው ረቡዕ ቀን ነው። ስለዚህ ኢየሱስ የተሰቀለበትን ቀን በዚህ መልኩ ማስላት ይቻላል ካለ በኋላ፤ ላለፉት 2000 ዓመታት የክርስትና እምነት ተከታዮችን ማነው ያታለላቸው? አምላክ? ወይስ ሰይጣን? የሚል ጥያቄ ለሚስተር ፋሂ ቀርቦለት ምንም ሳያቅማማ «ሰይጣን» ነው የሚል መልስ ሰጥቷል።

በዚህ ጊዜ ሸህ አህመድ ዲዳትና መሰሎቹ ስቅለትን ዓርብ ወይም ረቡዕ ማክበር በመሳሰሉት የእምነት ዘርፎች ላይ ሰይጣን ይህን ያህል



www.ethiopianorthodox.org

ውዥምብር በመፍጠር ከተሳካለት ፈጣሪን በተመለከተ በመሠረታዊው የእምነታቸው ጉዳይ ላይ ክርስቲያኖችን ማሳሳት ምን ያህል ቀላል እንደ ሚሆንላቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ፅንሰ ሐሳቡን የሸመደዱት ከደቡብ አፍሪቃው ደርባን ትምህርት ቤት ከሚስተር ሮበርት ፋሂ ነው። ከመምህሩ ይሻል ደቀ መዝሙሩ ነውና አህመድ ዲዳት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከሚስተር ፋሂ ባገኘው ሰይጣናዊ መላምት ተጠቅሞ ክርስቲያኖችን ለማሳሳት የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክና ቋንቋ የራሱ አድርጎ እየበረዘና እየከለሰ ፓንፍሌት ማሰራጨቱን በሰፊው ተያይዞታል።

ሚስተር ሮበርት ፋሂ የተባለው ደቡብ አፍሪቃዊ ፀረ–ማርያም እንደሚለው ክርስቲያኖች የስቅለትን ቀን ዓርብ እንዲያከብሩ ሰይጣን አላሳሳታቸውም፤ ዓርብን ወደ ረቡዕ እንዲቀይሩ ግን ሰይጣን በሚስተር ፋሂ ላይ አድሮ እየገፋፋቸው ነው፤ መናፍቃን ጦር መስበቅ ቢያስተምሩ እንጂ የድል ባለቤት ሊያደርጉ አይችሉም፤ ድል የእግዚአብሔር ነውና (መዝ.33፥16–17)።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ «ዮናስ በዓሣ ሆድ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ የሰው ልጅም በመቃብር ውስጥ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት ያድራል» ሲል ራሱ ባለ ቤቱ ባወቀ ወስኖና ለክቶ የተናገረውን ቀኖና ረዘመ ብሎ ማሳጠር አጠረ ብሎ ማስረዘም ቀኑንም ወደፊት ወደ ኋላ ማንከባለል አይቻልም፤ ሕገወጥነት ነው፤ ደግሞስ ቁም ነገሩን ማለት አዳኝነቱን አምላክነቱን የካደ መናፍቅ ክርስቶስ በመቃብር ውስጥ አንድ ቀን አደረ ሦስት ቀን ‹ዓርብ ይከበር ረቡዕ› እያለ የሚያወናብድ ማን አማካሪ አደረገው?



## ክፍል ሦስት

# ትንሣኤ ወይስ ማንሰራራት?

በዚህ ክፍል ውስጥ ጸሐፊው አንዳንድ ንዑሳን ክፍሎችን ደርድሮ ስለ ራሱ ገጠመኝና አንዳንድ ያላስፈላጊ መጠይቆች ብረዛዎችና ክለሳዎች ‹ድግግሞሾች› የበዙበት በመሆኑ መልስ ልሰጥበት አላተጋኝም።

ከንዑሳን ክፍሎች አንዱ ለሆነው ወደ መጨረሻው ላይ «ትንሣኤ የለም» ለሚለው ንዑስ ክፍል ብቻ አጭር ማብራሪያ እሰጥበታለሁ።

> «የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ እንዲህ ይላል፤ «እናንተ ክርስቲያኖች ምን ይሆን ችግራችሁ? ኢየሱስ ምንም በማያሻማ ቋንቋ መንፈስ እንዳልሆነ ወደ መንፈስነትም እንዳልተለወጠ ከሙታን ተለይቶ የተነሣ አካል እንዳልሆነ ይነግራችኋል፤ ግና የክርስቲያኑ ዓለም በሙሉ ኢየሱስ ከሙታን እንደ ተነሣ ወደ መንፈስነት እንደ ተለወጠ ያምናል፤ የዋሸው ማን ይሆን? ኢየሱስ ወይስ እናንተ? ኢየሱስ ስለ ትንሣኤው የሚሰጠው መልስ «በፍጹም አልተነሣሁም» የሚል ሲሆን እናንተ ክርስቲያኖች ደግሞ በአንፃሩ የምትሰጡት መልስ «በፍጹም ተነሥተሃል» የሚል ነው፤ እኛ ሙስሊሞች ማንኛችሁን እንቀበል? የኢየሱስን ቃል? ወይስ የደቀ መዛሙርቱን ጥርጣሬ? እኛስ የኢየሱስን ቃል መቀበል እንመርጣለን፤ ኢየሱስ ‹ደቀ መዝሙሩ ከመምህሩ...አይበልጥም› ብሎ አስተምሯልና» ተብሏል (ማቴ.10፥24)።

<u>ሐተታ</u>፤ ክርስቶስን በ30 ብር የሸጠው ደቀ መዝሙሩ ይሁዳ ጠቁሞ በአስያዘው ጊዜ መምህር ሆይ እንደምን ውለሃል? በማለት እጫማው ላይ ወድቆ ሰላምታ አቅርቦለታል፤ ክርስቶስም «ሰላምታ በመስጠት አሳልፈህ ልትሰጠኝ መጣህን?» ብሎታል፤ ሺህ አህመድ ዲዳትም ክርስቲያኖችን ምንድነው ችግራችሁ? በማለት ተቆርቋሪ ደቀ መዝሙር ‹አዛኝ ቅቤ አንጓች› መስሎ እየጠየቀ ቀርቧል።



www.ethiopianorthodox.org

ክርስትና ሳትነሣ ልታቋቁም ሄደች፣

የራሷ ሲያርባት የሌላውን ታማስላለች ይባላል።

ሸህ አህመድ ዲዳት መጀመሪያ በራስህ ዓይን ላይ ያለውን ስንጣሪ አውጣ፤ ከዚያ በኋላ በወንድምህ ‹በክርስቲያኑ› ዓይን ላይ ያለውን ጉድፍ ታወጣለታለህ፤ ላውጣልህ ትለዋለህ፤ «እኛ ሙስሊሞች ስለ ትንሣኤው የክርስቶስን ቃል ‹ምስክርነት› ነው የምንቀበለው» ካላችሁ፣ ከትንሣኤው በኋላ ሦስት ጊዜ እየተገለጠ ለሐዋርያት ታይቷቸዋል፣ «በመጀመሪያው ሳምንት ደቀ መዛሙርቱ አይሁድን ፈርተው በተከማቹበት ዝግ ቤት በመካከላቸው ተገኝቶ «ሰላም ለናንተ ይሁን ሲላቸው ለጊዜው ደነገጡ፣ መንፈስም መሰላቸው፣ እርሱ ግን ለምን በልባችሁ አሳብ ይወጣል ይወርዳል? እጄን እግሬን እዩኝ፣ እኔ ነኝና ዳሱኝ፣ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና» በማለት እጁን እግሩን አሳያቸው፣ በኋላም «ከዚህ አንዳች የሚበላ አላችሁን?» ሲል ጠየቃቸው፣ እነርሱም የተጠበሰ ዓሣና የማር ወለላ አቀረቡለት፣ ተቀብሎም በላ በፊታቸው ይላል።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞተ በኋላ በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ ቀደም ሲል ራሱ ያረጋገጠውና መጻሕፍትም የተነበዩለት ሐቅ ነው። ከትንሣኤው በኋላም በመካከላቸው ተገኝቶ የተቸነከረውን እጁን እግሩን በጦር የተወጋውን ጐኑን አሳይቷቸዋል፣ መንፈስም እንዳልሆነ አረጋግጦላቸዋል፣ እንደ ሰውነቱም በፊታቸው በልቷል ጠጥቷል፣ ቀደም ሲል ስለ ትንሣኤው የተናገሩትን መጻሕፍት እንዲያስተውሉ አእምሯቸውን ከፍቶላቸዋል፣ ከዚህ የተነሣ መምህራቸው ክርስቶስ መሆኑን ፈጽመው አምነውበታል፣ የክርስትናው ዓለምም የሐዋርያትን ዓይን ዓይን አድርጎ የሐዋርያትን እጅ እጅ አድርጎ ያለ ምንም ጥርጥር አምኖ ተቀብሎ በያመቱ ዓርብ ስቅለቱን እሑድ ትንሣኤውን እያከበረ 2000 ዓመታት አስቈጥሯል፤ የክርስትናው ዓለም በያመቱ ትንሣኤውን ሲያከብር የሚያሰማው መፈክር አለው።

«ክርስቶስ ትንሣኤ እሙታን፣ በዓቢይ ኃይል ወሥልጣን

አሰሮ ለሰይጣን፣ አግዓዞ ለአዳም፣ እምይዕዜሰ ኮነ ፍሥሐ ወሰላም»

ትርጓሜው «ክርስቶስ በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፣ ሰይጣንን አሰረው፣ አዳምንም ነጻ አወጣው፣ ከዛሬ ጀምሮ



ደስታና ሰላም ሆነ» ማለት ነው (ሉቃ.24፥36፤ ማቴ.12፥40፤ መዝ.12፥5፤ 78፥65)።

ረብ–የለሽ ድራማ ነው ተብሏል፣ ረብ–የለሽ ድራማ ማለት በማያውቁት የሃይማኖት ፍልስፍና ገብቶ ደቡብ አፍሪቃ ላይ መድረክ ከፍቶ ሕዝብን አሕዛብን ጠርቶ በክርስትና ሕይወት ላይ መዶለት ረብ–የለሽ ድራማ ነው። «እስከ ዓለም ፍጻሜ በዘመኑ ሁሉ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴ.28፥20)።

## ልዩ ማስገንዘቢያ

«የአብ ቃል (የአላህ ቃል) ለምን ሰው ሆነን»

«አስቀድሞ ቃል ነበር ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ቃልም እግዚአብሔር ነበር፤ ሁሉ በእርሱ ሆነ ያለ እርሱ ምንም ምንም የሆነ (የተፈጠረ) የለም፤ ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም ላይ አደረ» (ዮሐ.1፥1–14፤ ጢሞ.3፥16)። ቁርአንም በኩሉ «መርየም ሆይ! አላህ ከርሱ በኾነው ቃል፣ ስሙ አልመሲሕ ዒሳ የመርየም ልጅ፣ በዚህ ዓለምና በመጨረሻውም ዓለም የተከበረ ከባለሟሎችም በኾነ (ልጅ) ያበስርሻል» ይላል (ቁርአን ምዕ 3፥45)።

የሰው ዘር እናትና አባት አዳምና ሔዋን መሆናቸውን የማያውቅ የለም። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን በመልኩና በምሳሌው ከፈጠራቸው በኋላ በገነት ቦታቸውን ወስኖ፣ የሚበሉትንና የሚጠጡት አዘጋጅቶ፣ ሕግና ሥርዓት ሰጥቶ የፈጠራቸውን አምላክ የሚያመሰግኑበት የጸሎት ሰዓት ለይቶ አስቀመጣቸው።

በገነት ውስጥ ሦስት እንጨቶች ነበሩ። አንዳ ምግቡ ነው፤ ሁለተኛው ዕፀ በለስ ነው፤ ሦስተኛው ዕፀ ሕይወት ይባላል። ከነዚህ ከሦስት አንዷቱ ዕፀ በለስ የፍጡርና የፈጣሪ የገዥና የተገዥ ምልክት (አታድርግ የምትል ሕግ) ነበረች። አዳምና ሔዋን በዕፀ በለስ አምካይነት የተሰጣቸውን ሕግ ጠብቀው ለሰባት ዓመታት ያህል በገነት ኖሩ። ከሰባት



www.ethiopianorthodox.org

ዓመታት በኋላ ግን በሰይጣን ተታለው ዕፀ በለስን በሉ፤ ከፈጣሪያቸው ተጣሉ፤ ከገነት ወጡ፤ ክብራቸውን አጡ።

ታዲያ አዳምና ሔዋን ከፈጣሪያቸው ተጣልተው ከገነት ወጥተው ቀሩ ወይስ ይቅርታ አግኝተዋል? ይቅርታ ካገኙስ እንዴት ሊያገኙ ቻሉ? ይህ ጥያቄ በሙስሊሙ ኅብረተሰብ ምሑራን ዘንድ ተገቢ ትኩረት ያልተሰጠውና እስከ ዛሬም መልስ ሊያገኝ ያልቻለ ዓቢይ ቁም ነገር ነው። እንደ ሐዲስ ኪዳን አነጋገር የአብ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ቁርአን ደግሞ ‹የአላህ የሁን ቃል አልመሲሕ ለምን ሰው ሆነ? የሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም። የአብ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነበት ምክንያት ከላይ እንደ ተገለጠው አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን በልተው ከፈጣሪያቸው ተጣልተው ከገነት በመውጣታቸው የመረረውን ልቅሶ አለቀሱ፤ ፍጠረን ሳይሉት የፈጠራቸው አምላክ ለቅሷቸውን ሰምቶ አዘናቸውን ተመልክቶ «በአምስት ቀን ተኩል መጥቼ አድንሃለሁ» የሚል ተስፋ ሰጠው። አምስት ቀን ተኩል ማለት አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ማለት ነው። አምሰት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ በመስቀል ላይ ሞቼ ተነሥቼ አድንሃለሁ ሲለው ነው። «ወዳጆች ሆይ፣ አንድ ቀን በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ሺህ ዓመት ነውና ሺህ ዓመትም እንዳንድ ቀን፣ የእግዚአብሔር ተስፋ አይዘገይም ሰዎች ይዘገያል እንደሚመስላቸው፤ ነገር ግን እርሱ ይታገሠናል፣ ማንም ቢጠፋ አይወድምና ሁሉም ወደ ንስሐ ይመጡ ዘንድ ይወዳል እንጂ (2ጴጥ.3፥8–9)።

ተናግሮ የማያስቀር የሰጠውን ተስፋ የማያጥፍ አምላክ ከመውረዱና ከመወለዱ በፊት ይወርዳል ይወለዳል ሲሉ ነቢያት ትንቢት ተናግረዋል። ከነዚህም አንዱ ኢሳይያስ፣ «ድንግል በድንግልና ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» ብሎአል፣ ዳንኤልም «እስከ መሲሕ (ክርስቶስ) ድረስ ቤተ መቅደስ (ኢየሩሳሌም) ትሠራለች» ብሎአል፣ ጊዜው ሲደርስ ደግሞ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል «እነሆ ትፀንሻለሽ፣ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፣ ስሙንም ኢየሱስ ብለሽ ትጠሪዋለሽ፣ የልዑል ልጅም ይባላል፣ እግዚአብሔር አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፣ በያዕቆብ ወገን ለዘላለም ይነግሣል፣ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም፣ ሲል ለድንግል ማርያም አብሥሮአታል» (ኢሳ.7፥14፤ ዳን.9፥25፤ ሉቃ.1፥28)።

ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክ ስለ መሆኑ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ በተጠመቀ፣ ጊዜ «እነሆ ሰማዮች ተከፈቱ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ተቀመጠ፤ ከሰማይም ድምፅ መጣ፣ እንዲህ ሲል:- «የምወደው ደስታዬንም የምገልጽበት ልጄ ይህ ነው» (ማቴ.3፥16፣ 17፥5)።

«እግዚአብሔር እንዲሁ ዓለሙን ወዶአልና አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ በርሱ ያመነ ሁሉ እንዳይጠፋ የዘላለም ሕይወት ትሆንለት ዘንድ እንጂ፣ እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም አላከውምና ዓለምን ሊኮንን፣ ነገር ግን ዓለም ይድንበት ዘንድ እንጂ ነው፣ በርሱ ያመነ አይኮነንም፣ የማያምንበት ግን አሁን የተኮነነ ነው! በአንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም አላመነምና» (ዮሐ.3፥16–18)።

«በዚህም የእግዚአብሔር ፍቅር ተገለጸ፣ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ እኛ ወደ ዓለም ልኮታልና፣ በእርሱ እንድንበት ዘንድ» (1ዮሐ.4፥9)። እንግዲህ አብ እና ወልድ ! አባትና ልጅ ከዛሬ 1990 ዓ.ም ገደማ ላይ በክርስትናው ዓለም አደባባይ እጅ ለእጅ ተያይዘው አባትና ልጅነታቸውን አምነው ሕልውናቸውን ያረጋገጡበት ሰነድ (ሐዲስ ኪዳን) የማያወላውል ማስረጃ ነው። ከጐረቤት አንድ ሰው ተነሥቶ አንተ አባቱ አይደለህም፣ አንተም ልጁ አይደለህም ሰነዱም ትክክል አይደለም በማለት ለማስተባበል ቢሞክር ምን ይባላል? «ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው» ከምንለው በስተቀር ሌላ ምን ይባላል? የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስም የአብ ልጅነቱን በሥጋ ተገልጦ አምላክነቱን በሥራ አረጋግጦ ወደ ሰማይ ካረገ ከ600 ዓመተ ምሕረት በኋላ እስልምና ተነሥቶ፣ «አላህ አንድ ነው፣ አይወርድም አይወለድም ሸሪክ የለውም» በማለት ለክርስትናው ዓለም ሊሰብክ ቢሞክር አሁንም «ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው» ወይም «ምጥ ለእናቷ አስተማረች»



www.ethiopianorthodox.org

እንለዋለን። የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክ ስለ መሆኑ ማስረጃው ሐዲስ ኪዳን ነው። የሙስሊሙ አፈ ቀላጤዎች ግን ይህ ሐቅ አይዋጥላቸውም። ሙስሊሞች የሚሟገቱት ከክርስቲያኖች ጋር ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ነው። ስለዚህ የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነቱን እና አዳኝነቱን ይግለጽላችሁ፤ ሰሚ ጆሮ ማስተዋያ አእምሮ ይስጣችሁ።

«የክርስቶስን ትምህርት ይለውጡ ዘንድ ሰዎች ያውኩአችኋል፣ ነገር ግን እኛም ከአስተማርናችሁ ሌላ መልአክ ከሰማይ ወርዶ ቢያስተምራችሁ ውጉዝ የተለየ ይሁን» (ገላ.1፥8፤ 1ቆሮ.16፥22)።

«ወስብሐት ለእግዚአብሔር»

አነሣሥቶ ላስጀመረኝ አስጀምሮ ላስፈጸመኝ አምላክ ክብር ምስጋና ይግባው፣ አሜን።

## አከፋፋዮች

ደስታ የጽሕፈትና መጽሐፍ ድርጅት

011 552 17 00

ዋሸራ መጽሐፍት መደብር

011 276 89 40

0911 43 29 40





መምህር ኪዳነ ማርያም ጌታሁን

www.ethiopianorthodox.org